# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና የል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅ ርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀ ረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመ ረዳት ይቻላል ።


የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቁ. 116616
የመል. ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ትንሣኤ



“ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ሆይ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑሻል ።”


ዋጋው ሃምሳ ሣንቲም ቁጥር 47 ነሐሴ ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.



www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ሲሠራ እንነግ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።


አዘጋጅ
ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
ም/አዘጋጅ ራደ አስረስ ።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


# ማውጫ

ገጽ

አርእስት


ደብዳቤዎች ........ 4
እናትነት ከድንግልና ........ 5
ኅብረተ ሰብእና ባሕል ........ 6
ሙታን ድምፁን ይሰማሉ ........ 7
የክብሩ ብርሃን ታላቅነት ........ 8
የሴቶች ዓምድ ........ 10
በመንፈስ ለሞቱ የትምህርት ትንሣኤ ........ 11
ምን እንርዳዎ ? ........ 13
ይህን ያውቁ ኖሯል ? ........ 14
ዜና ሊቃውንት ........ 16
ከቤተ ክርስቲያን የቋሪኪ ዓምድ ........ 17
የቤተሰብ ዓምድ ........ 18
ቅዱስ ሩፋኤል ........ 22




የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ፩ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በጸሎትና በታላቅ ሥነ ሥርዓት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም. በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ይከበራል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ርእሰ አንቀጽ

# “ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ”

“ኦርቶዶክስ” የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙ ርትዕት ሃይማኖት የቀናች የጸናች ሃይማኖት ማለት ነው ።
በዚህ ስያሜ የኦርቶዶክስና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይጠሩበታል ።
በዚህ ስያሜ የኦርቶዶክስና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ይጠሩበታል ።

“ ተዋሕዶ” ይህ ቃል ተዋሐደ አንድ ሆነ ከሚለው የግእዝ ቃል (ግሥ) የተገኘ ዘር ነው ። ይህም አንዱ ባሕርይ ከሌላው ባሕርይ ጋር ተስማማ ፣ ተዋሐደ አንድ ሆነ ማለት ነው ።

“ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ” የሚለው ጣምራ ስያሜ ግን ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ከምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ተለይተው የሚጠሩበት ልዩ ቅጽል ነው ። ይኸውም የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት “ኦርቶዶክስ” ብቻ ተብለው ሲጠሩ የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ግን “ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ” ተብለው ይጠራሉ ።

እነርሱም ሀ- የኮፕት ለ- የሶርያ (ያዕቆባዊት) ሐ- የአርመን መ- የኢትዮጵያ

ሠ- የሕንድ (ማላባር) አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ።

ይህም ልዩነት የመጣው በ4ኛ ጉባኤ በጉባኤ ኬልቄዶን እ.ኤ.አ. በ451 ዓ.ም. በአብያተ ክርስቲያናት መካከል በተፈጠረው አለመግባባት የምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ አንድ አካል ሁለት ባሕርይ ነው ሲሉ የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ግን አካላዊ ቃል ሥጋን በተዋሐደ ጊዜ ባሕርየ መለኮት የሥጋ ፣ ባሕርየ ሥጋም የመለኮት ገንዘብ ሆኖአል ስለሆነም ክርስቶስ በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው እንጅ ሁለት ባሕርይ አይደለም በማለት ስለተለዩ ነው ።

ቀዳማዊ ቃል ባሕርዩን ቀዳማዊነቱን ፣ ምልዓቱን ርቀቱን ሕያውነቱን ሳይተው በማኅፀነ ማርያም ነፍ ስንና ሥጋን ተዋሐደ የሥጋን ባሕርይ ገንዘብ አደረገ ወልደ አብ አካላዊ ቃል በተዋሕዶተ ሥጋ ወልደ ማርያም (የማርያም ልጅ)ተባለ ። ፍጡራዊ ሥጋም ባሕርዩን ሃ:ጎራዊነቱን ፣ ውሱንነቱን ፣ ግዙፍነቱንና መዋቲነቱን ሳይተው በተዋሕዶተ መለኮት ቀዳማዊ አምላክ ሆነ አምላክ ፣ ወልደ አምላክ ተባለ ባሕርየ መለኮትን ገንዘብ አደረገ ። ቅድመ ዓለም የነበረ የእግዚአብሔር ቃል በሕርይና የፍጡራዊ ሥጋ ባሕርይ በግብረ መንፈስ ቅዱስ በማኅፀነ ድንግል ተዋሐደ ፣ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ፡ መለኮት በተዋሕዶ የሥጋን ባሕርይ ገንዘብ አድ ርጐ ፍጹም ሰው ሆነ ሥጋም በተዋሕዶ የመለኮትን ባሕርይ ገንዘብ አድርጐ ፍጹም አምላክ ሆነ በተዋሕዶ ከበ ረ የመለኮትንና የሥጋን ተዋሕዶ ሊቃውንት በሚከተሉት ምሳሌዎች ያስረዳሉ ።

1- የብረትና የእሳት ተዋሕዶ ፣ ብረቱን በእሳት መካከል ጥለው በወናፍ ሲያናፉት ብረቱ እሳቱን ይመስ ላል በመዶሻ ሲመቱት በእሳት ተዋሕዶነት ብረቱ ተቀጥቅጦና ተጨፍልቆ ለተፈለገው ሥራ ይውላል ፡ ይህንን ቅዱስ ቄርሎስ በሚከተለው ሁኔታ ገልጦታል።“በእግዚአብሔር ቃል በረቂቅ ባሕርይ የሆነውን ተዋሕዶ እን ካድ ፣ ብረት ከእሳት በተዋሐደ ጊዜ ፣ ከእሳት በመዋሐድ የእሳትን ባሕርይ ገንዘብ እንዲያደርግ ፣ ብረት በመዶሻ በተመታ ጊዜ ከእሳት ጋር በአንድነት እንደሚመታ ፣ ግን ከመዶሻው የተነሣ የእሳት ባሕርይ በምንም በምን እንዳይጐዳ ሰው የሆነ አምላክ ቃል በመለኮቱ ሕማም ሳይኖርበት በሥጋ እንደ ታመመ እንዲህ እናስተውል” (ሃይማኖተ አበው ም ፡፡70ቁ ፡ 12 ፣ 12)

2- የዐይንና የብርሃን ተዋሕዶ ብርሃን ከዓይን ጋር በመዋሐድ በጨለማ ተሸፍኖ ፣ ተውጦና ተሰውሮ የነ በረውን ልዩ ልዩ ዕቃ ለማየት ያስችላል ፣ የመለኮትና የትስብእት ተዋሕዶ በዚህና በመሳሰሉት ምሳሌዎች ይገ ለጥ እንጂ ምሳሌው ፣ ምሳሌ ዘየሐፅፅ መሆኑን ማስተዋል ይገባል ለዚህ አምላካዊ ምሥጢር (ትምህርት) ትክክ ለኛና በቂ ምሳሌ ሊገኝ አይችልምና ።

ታዲያ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት እምነትና ትምህርት ይህ ሁኖ ሳለ ፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ያውጣዕኬን ትምህርት እንደ ተከተሉ በመገመት የሥጋ ባሕርይ ጠፍቶ የመለኮት ባሕርይ ብቻ እንዳለ ያምናሉ ሲሉ “ሞኖፊስት” ይሏቸዋል ““ሞኖ” በግሪክ ነጠላ ማለት ሲሆን (ሞኖፊስት) በነጠላ ባሕርይ የሚያምኑ ማለት ነው ።

አባባሉ ግን ልክ አይደለም ። የኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ክርስቶስ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ነው ብለው ያምናሉ ። ስለሆነም መለኮት ባሕርዩን ቀዳማዊነቱን ምልዓቱን ፣ ስፋቱን ፣ ርቀቱን ፣ ኃያልነቱንና

www.ethiopianorthodox.org

ሕያውነቱን ሳይለቅ ፡ ሥጋም ባሕርዩን ደኃራዊነቱን ውሱንነቱን ግዙፍነቱንና መዋቲነቱን ሳይተው በመዋ
ሐድ አንድ አካል አንድ ባሕርይ ሆነ ።
በዚህ ተዋሕዶ የመለኮት ባሕርይ ለሥጋ ፣ የሥጋም ባሕርይ ለመለኮት ገንዘቡ ነው ። "ዘኢአሁ ለቃል
ኮነ ለሥጋ ወዘኢአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል" ፣ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋም ገንዘብ ለቃል ሆነ ተብሎ ተጽፎአልና
ስለዚህ በባሕርዩ መወሰን ፣ መራብ ፣መ ጠማት ፣ መታመምና መሞት ያልነበረበት መለኮት በተዋ
ሕዶተ ሥጋ በጠባብ ደረት በአጭር ቁመት ተወስኖ ታየ በሥጋ ተራበ ተጠማ ፣ ታመመ ሞተ ። ረኃብና ጽም
ሕማምና ሞት የባሕርዩ የነበረ ሥጋም ባሕርየ መለኮትን ስለተዋሐደና ከመለኮት ጋር አንድ አካል አንድ ባሕ
ርይ ስለሆነ 40 ቀን ረኃብንና ጽምዕን ታገሠ ከሞተም በኋላ በተዋሕዶተ መለኮት ሙስና መቃብርን አጥፍቶ
ሞትን ድል ነሥቶ ተነሣ ወደ ሰማይም ዓረገ ብለው ያምናሉ እንጂ አንዱን ትተው ሌላውን ይዘው ሌሎች "ሞ
ኖፊስት" እንደሚሉአቸው በነጠላ ባሕርይ አያምኑም ዮሐ 1 ፣ 14 ፣ 3 ፣ 13 ፣ ኤፌ. 4 ፣ 9 ፣ 1ጴጥ. 3 ፣ 18 ።
ስለዚህ "ሞኖፊስት" የሚለው ቃል (ስያሜ) ለኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት መጠሪያ ስም ወይም
ቅጽል አይደለም ። እንዲህ ከሆነ አንዱን ባሕርይ አጥፍቶ ሌላውን ያልተቀበለውን እምነት "ሞኖፊስት" ብሎ
መጥራት እንዴት ይቻላል ? ምን አልባት በአምስተኛው መቶ ዘመን በስሕተት በታሪክ የተመዘገበ የሽሙጥ
ስም ይሆናል እንጂ የእነርሱ መጠሪያ አለመሆኑን መገንዘብ ይገባል ። በማያምኑበት ስያሜ ሊጠሩበት አይችሉ
ምና ።

# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ

አ.አ

የግእዝ ቋንቋ ለቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ መሣሪያ ሲሆን ለአማርኛችንም መጋቢ ነው ለዘመኑ ሳይንሳዊ አነጋገርም ጥልቀትና ስፋት ያላቸውን የጥቅለላና የትንተና ቃላት በመለገስ (በማዋስ) ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረገና የሚያደርግ ነው ። ስለዚህም አዲሱ ትውልድ በመክሰም ላይ ያለውን የግእዝ ቋንቋ እንዲማረውና እንዲመራመረው ቢደረግ ለኅብረተ ሰቡ ከፍተኛ ጥቅም ከመስጠቱም ሌላ ቋንቋውም ሕያው ይሆናል ።

ታዲያ ይህን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት የካሤት ሐዋርያ አገልግሎት የግእዝ ቋንቋ ትምህርትን በካሤት እንደሚያሠራጭ ሁሉ በትንሣኤ መጽሔትም ለግእዝ ቋንቋ መልመጃ ዓምድ ቢከፍትና ተከታታይ ትምህርት ቢሰጥ የግእዝ ቋንቋን ከዘመኑ ትውልድ ጋር ከማስተዋወቁ በላይ መጽሔቱንም ተወዳጅ እንደሚያደርገው እገምታለሁ ።

ለንባቡ አነሣሥና አጣጣል ሲባል ደግሞ የካሤቱንም ተፈላጊነት ያበዛዋል ።

ስለዚህ ጥያቄው ለትንሣኤ አንባቢዎች ቀርቦ ሐሳብ እንዲሰጡበት ቢደረግና የአንባቢዎቹ ድጋፍና ተቃውሞ ተመዝኖ ፣ የቤተ ክርስቲያን ምሑራንም ነገሩን ቸል ሳትሉ ብትመካከሩበትና ነገሩ በጎ ሆኖ ቢታያችሁ እንደ ጥያቄዬ ቢፈጸም መልካም ይመስለኛል እናንተስ ምን ይመስላችኋል ?

በተረፈ ግን ኃይለ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን

የመጽሔታችሁ ወዳጅ የክርስቶስ ባሪያ

ወታደር አራጋው መኩሪያ

መ.ሣ.ቁ. 42 ሐረር

● ወታደር አራጋው መኩሪያ ስለላኩልን ጥያቄና አስተያየት ጥልቅ ምስጋና እናቀርባለን ያቀረቡልን ጥያቄዎች ስድስት ሲሆኑ በዚህ እትም ያወጣነው አንዱን ብቻ ነው ፣ ምክንያቱም ስድስቱን ጥያቄዎች በአንድ ጊዜ ለመመለስ ዓምድ ስለጠበበን ጥያቄዎቹን በተራ ለመመለስ አስበን ነው ።

በትንሣኤ መጽሔት የተለየ [illegible] ሰጥተን የግዕዝ ትምህርት እንድናስተላልፍ እንደእርስዎ በርከት ያሉ ሰዎች ጠይቀውናል አስፈላጊና ጠቃሚ መሆኑን እኛም እናምናለን ። ስለዚህ በጠየቁት መሠረት የትንሣኤ ደንበኞች ሐሳብ እንዲሰጡበት የእርስዎን አስተያየት በሙሉ በዚህ እትም አውጥተነዋል ። ለእርስዎም አስተያየት ድጋፍ እንጂ ተቃውሞ ይመጣል ብለን አንገምትም ስለሆነም ከዚህ እትም በኋላ የሚደርሱንን አስተያየቶች ገምግመን ትንሣኤ የግእዝ ቋንቋ ዓምድ እንዲኖረው ለማድረግ ዝግጁዎች ነን ።

•••

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር 44 ተሾመ ካሣሁን ካቀረባቸው 10 ጥያቄዎች 7ኛው "በጠቅላይ ቤተ ክህነት የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊ በየመንፈሳውያን ወጣት ማኅበራት እየተዘዋወሩ ችግሮችን ለምን አይመለከቱም ?" የሚል ነበር ትንሣኤም የወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ችግር ያለባቸውን የመንፈሳውያን ወጣቶች ማኅበራት ቦታዎች ከተረዳ እየተዘዋወረ ችግሮችን የመፍታት ኃላፊነት ያለበት መሆኑ ጠቁሞ

ወደ ገጽ ፮ ዞሯል

# እናትነት ከድንግልና

በሥነ ፍጥረት ሕግ ሁለት የማይስማሙ (ተቃራኒ) ነገሮች በአንድ ጊዜ በአንድነት አይታዩም ፣ አንዱ ሌላውን አስለቅቆ ይታያል እንጂ ለምሳሌ ብርሃን ሳለ ጨለማ ፤ ቅዝቃዜ እያለ ሙቀት አይኖርም ። እንዲሁም በሰው ልጆች ሕይወት ፣ ሕፃንነትና ሽምግልና ፣ እናትነትና ድንግልና የመሳሰሉት ሁሉ አንዱ ከሌላው ቀጥሎ የሚመጣ እንጂ ሕፃን ሲሆን ሽማግሌ የሆነ የለም እናት ስትሆን ድንግል የሆነችም የለችም ቅድመ ዓለም የነበረ የአብ አካላዊ ቃልን ከወለደች ከድንግል ማርያም በቀር ።



ድንግል ማርያም ምስለ ፍቁር ወልዳ

የሰው ልጆች ወንዱ ለአቅመ አዳም ሴትዋ ለአቅመ ሔዋን እስኪደርሱ በድንግልና ይኖራሉ ፤ ለአካለ መጠን ሲደርሱ ወንዱ ሚስት ፣ ሴትዋ ባል ሲያገቡ ድንግል መባላቸው ይቀራል ሴቶች ሁሉ ለአቅመ ሔዋን እስኪደርሱ በድንግልና ይኖራሉ ባል ከአገቡና ልጅ ከወለዱ በኋላ ደናግል መባላቸው ይቀራል ልማደ አንስት ዘርአ ወራዙት ያርሶአቸው እናቶች ሆነዋልና ። ስለሆነም እናትነትና ድንግልና በአንዲት ሴት ሕይወት ላይ በአንድነት ሊኖሩ የማይችሉና የማይስማሙ ሁኔታዎች ናቸው ። የእናትነት ሥራ ድንግልናን ያስወግዳል ፣ ድንግልናም እናት ለመሆን አያበቃም ።

በድንግልና እናት ለመሆን የበቃች ከእናትነትም ጋር ድንግልናን አስተባብራ ይዛ የተገኘች ከቅድስት ድንግል ማርያም በቀር ሌላ ሴት የለችም ። ያለ ዘርአ ብእሲ በድንግልና ልጅ መውለድና በድንግልና ጸንቶ መኖር "ድንግል ወእም" መባል ግን ከተፈጥሮ ሕግ በላይ የሆነ አስደናቂና አምላካዊ ምሥጢር ነው ።

ይህ ምሥጢር ቀደም ሲል በምሳሌ ተገልጦአል በትንቢትም ተነግሮአል ። ምሳሌ የአዳም ከጎኑም ምድር ፣ የሔዋንም ከጎኑም አጽመ ገቦ መፈጠር አካላዊ ቃል በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና ለመወለዱ ምሳሌ ነው ። ዘፍ 2 ፥7-24 ይህን ምሥጢር ዮሐንስ አፈወርቅ በሚከተለው ሁኔታ አብራርቶ ገልጾታል ። "ቀድሞ አዳምን ካልታረሰች (ከድንግል) ምድር ፈጠረው ዳግመኛ ሔዋንን ከአዳም ያለ እናት ፈጠረ ። አዳም ያለ እናት ሔዋንን እንዳስገኘ እንዲሁ ዛሬ ድንግል ክርስቶስን ያለ አባት ወለደች" (ሃይ አበ ክፍ 9 ፥28) "ከአዳም ጎን የጐድን አጥንት እንደ ነሣ አዳምንም አካል እንዳልጐደለው እንዲሁ ከድንግል የምትናገርና የምታውቅ ነፍስ ያለችው ሥጋን ተዋሕዶ ማሕተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ። አዳም የጐድን አጥንት ከእርሱ ከተነሣ በኋላ አካል ሳይጐድለው ፍጹም ሆኖ ኖረ ። ድንግልም ሕፃን ክርስቶስ ከእርስዋ ከተወለደ በኋላ እንዲሁ ያለ መለወጥ በድንግልና ጸንታ ኖረች ።



(ሃይ አበ ም ፡ 66 ክ ፡ 9 ፥3

እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆኑ አምላክነቱን አላስቀረበትም ድንግል ማርያምም እናትነትዋ ድንግልናዋን አላስቀረባትም ። ስለሆነም እርስዋ ድንግል ወእም" "ስትባል መኖርዋ እርሱ "አምላክ ወሰብእ" ሲባል ለመኖሩ ማስረጃ ነው ። ይህንንም ሊቁ በሚከተለው ገልጾታል "በወለደችውም ጊዜ ድንግልናዋን ያለመለወጥ አጸና ፤ ድንቅ በሚሆን ጽንስዋ ለደገኛው ሃይማኖት መሪ ትሆን ዘንድ" (ዮሐንስ አፈወርቅ ሃይማኖተ አበው ም፥66 ክ 9፥32) "የእናቱን ማኅፀን የፈጠረ ድንግልናዋንም ያጸና እርሱ ነው ፣ ዘር በሌለበት ልደት ተወልዶአልና ።" ቁ 34 "የአምላክ ሥራ ስለሆነ መጽነስዋ በጣም ይደንቃል የመውለድዋ ምሥጢር ኃይልም አይመረመርም ። ማንም ማን ባሕርይውን የማያውቀውን እርሱን ወለደችው ማኅተመ ድንግልናዋም አልተለወጠም ። (ጎርጎርዮስ ሃይማኖተ አበው ም፡ 60 ክ ፡ 1፥ 15) "ከድንግል ብቻ ተወለደ ድንግልናዋንም ያለመለወጥ አጸና" ቁጥ. 20 "ከእናቱ በድንግልና ተወለደ በመወለዱም ድንግልናዋ አልተለወጠም የወሰነችው የድንግል ማኅፀን አልተለወጠም እንደ ቀደመው አጸናት እንጂ፥ (ጎር ሃይማኖተ አበው ም፥ 61 ክ 3 ፥6) "በድንግልና ሳለች ከእርስዋ ተወለደ ድንግል ማርያምን እናቱ አላት ከፈጠራት ጀምሮ በምንም በምን ከድንግልናዋ አልተለወጠችም" (ቴዎዶጦስ ሃይማኖተ አበው ም፥ 53 ክ ፡ 1 - 22

በትንቢትም አካላዊ ቃል ከድንግል እንደሚወለድ እርስዋም በድንግልና ጸንታ እንደምትኖር ኢሳይያስ "እነሆ ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች"በማለት ትንቢት ተናግሮ ነበር ኢሳ. 7 ፡ 14 ። ሕዝቅኤልም በራእዩ

ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል

www.ethiopianorthodox.org

## ደብዳቤዎች...

ከገጽ ፬ የዞረ

ለጥያቄውም መልስ እንዲሰጥ ባሳሰበው መሠረት መምሪያው የሚከተለውን መልስ ሰጥቶአል ።

ጠያቂው ከሰንበት ት/ቤት ወይም ከሰበካ ጉባኤ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አንዱ አባል ከሆኑ ጥያቄውን ራሳቸው ሊመልሱት ይችላሉ ካልሆኑ ግን መልሱ ይህ ነው ።

በእያንዳንዱ የሰንበት ት/ቤት ላይ የሚደርሰውን ችግር በቅርብ ሊያውቀውና መፍትሔም ሊሰጠው የሚችል ያጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት ነው ይህም ሲባል እንደ ችግሩ ክብደትና ቀላልነት ነው፡፡ሌላው ችግር ደግሞ በሰንበት ት/ቤት አባላት መካከል በአንዳንዶቹ ላይ የጠባይ መታወክ ሲደርስ ነው ። ይህም ቢሆን በሰንበት ት/ቤቱ መምህርና በሰበካ ጉባዔው አማካይነት ሊወገድ የሚችል ሲሆን በአጠቃላይ በሰንበት ት/ቤት የሚደርሰውን ችግር በቅድሚያ መፍታት ያለበት ሰበካ ጉባኤው ነው ። የማይቻል ከሆነም ጉዳዩን ወደ ወጣቶች ጉዳይ መምሪያ ተላልፎ መፍትሔ እንዲገኝለት ይሆናል በተጨማሪም በይበልጥ ለመረዳት የ1973 ዓ.ም. የሰንበት ት/ቤቶችን መመሪያ ውስጠ ደንብ ምዕራፍ 3 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 2 ፣ ምዕራፍ 7 አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 1 ፣ 2 ፣ 3 ይመልከቱ ።

ከወጣቶች ጉዳይ መምሪያ

## የከንባታና ሐዲያ ብሔረ ሰቦች ባህል

የሸዋ ክፍለ ሀገር አሥራ አንድ አውራጃዎች እንዳሉት ግልጽ ነው ። ከነዚህ ከአሥራ አንዱ ውስጥ የከምባታና ሃድያ አውራጃ አንዱ ነው ።

የከምባታና ሃዲያ አውራጃ ካለው ተስማሚ የአየር ንብረት ጋር ለም በመሆኑ መሬቱ ለእርሻ የተስማማ ነው ። ምንም እንኳን በተለይም በደጋው አካባቢ እንሰት ሰፊ የጓሮ አትክልትና ለምግብነትም የሚያገለግል አስተማማኝ ተክል ቢሆንም ፣ በአውራጃው ውስጥ ልዩ ልዩ ጥራጥሬዎች ጤፍ ከቅመማቅመምም ዓይነት ዝንጅብል እንዲሁም ለአገር ውስጥና ለውጭ አገር ገበያዎች የሚቀርብ ቡና ይመረታል ። ሕዝቡ ለእርሻ ተግባር በበሬዎች ቢጠቀምም በደጋውና በተራራማው አካባቢ ተረተሮችን የሚቆፍረው የእጅ የማምረቻ መሣሪያ በሆነው ሆርዳ ወይም በብሔረሰቦቹ መጠሪያ ወንቾ በሚሉት እንደ አንካሴ ዓይነት ነው ። ነገር ግን ከወፍራም አጠና በተሰራ እጀታ ፣ እጀታውም ከታች መንታ ጫፎች ተደርገውለት ሁለት ሹል ማረሻዎች በተሰኩበት የቁም መቆፈሪያ ነው ። የከምባታና ሃዲያ ብሔረሰቦች ሥራ ወዳዶች ስለሆኑ በማለዳ ተነስተው በሥራ አገዛዘፊን እየተረዱ በዚሁ ዓይነት የሚያያዙትን ቁፋሮ ያከናውናሉ ።

አውራጃው ለም ቢሆንም የኑዋሪው ብዛት ከሁለት ሚሊዮን አያንስም በአጠቃላይ በአውራጃው ስምንት ልዩ ልዩ ብሔረሰቦች በወንድማማችነት ተሳስበው ይኖራሉ ። እነርሱም ፣ ከምባታ ፣ ሃዲያ አዘርነት (በርበሬ) ወላይታ ጉራጌ ፣ እንደጋኝ ፣ አላባና ኦሮሞ ብሔረሰቦች ናቸው ።

### የቤተሰብ አኗኗር

በከምባታና ሃዲያ ብሔረሰቦች ዘንድ የቤተሰብ አቋም የተከበረ ነው ። ሽማግሎች ልጆቻቸውን ባለው መሠረት የባህል መርህ ያሳድጋሉ ይድራሉ ይኩላሉ ወጣቶችም በበኩላቸው የሚፈለግባቸውን ሥነ ሥርዓት በመጠበቅ ከኅብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ ሳይወጡ በአክብሮት ይረዱዋቸዋል ።

በብሔረሰቦቹ ዘንድ በአንድ ቤት ውስጥ ወላጆች ከልጆቻቸው ጋር መኖር የተለመደ ቢሆንም የልጆቻቸውን እንክብካቤ የሚሹ የሸመገሉ ወላጆች በልጆቻቸው ቤት እየኖሩ ይጦራሉ ። ለትዳር የበቁ ወጣቶች አብዛኞቹ ቤት ሠርተው የሚኖሩት በወላጆቻቸው ቁዬ አጠገብ ስለሆነ በእርጅና ዘመን ሽማግሌ ወላጆቻቸውን ለመንከባከብ ችግር እያጋጥማቸውም ።

የከንባታና ሃዲያ ብሔረ ሰቦች ጠንካራና ጽዱ ቤቶች ሰርተው ይኖራሉ ፣ ቤቶቻቸውም ግድግዳዎቻቸው ከእንጨት ቋሚዎችና ከወፍራም ቀርቀሐዎች ይሠሩና ጣራዎቻቸው በተሰነጠቁ የቀርቀሐ ወራጆች ችምችም ተደርገው ይሠራሉ ። ያ በሣር ይከፈከፋል ። አርጅተው እስከወደቁ ድረስ ፍሳሽ የሚባል ነገር የለም አንዳንዶቹ እነዚህን ቤቶች ለሰው መኖሪያ ፣ ለማብሰያና እልፍም ብሎ ለምርጥ የቀንድ ከብቶች ማሠሪያ ጋጣ ያደርጉለታል ። ሌሎች ደግሞ አንድ ዋና ቤትና በአጠገቡ አንድ ያማረ የእንግዳ መቀበያ ወይም የቤተሰብ መዝናኛ ይሠራሉ በብልህ የባህል እቃ አናጢዎች የተሰሩ መቀመጫዎች በሳሎኑ ውስጥ ሲታዩ ፣ የተዋቡ የእንጨትና የሸክላ ቁሳቁሶች በግድግዳ ላይ ማንጠልጠልም የተለመደ ነው ። የከምባታና ሃዲያ ብሔረሰቦች ቤት ሲሰሩ በቤታቸው ፊትለፊት በዛፎች የተከበበ መስከ መተው ባህላቸው ነው ። ይህ መስከም በሸንጎ ወቅት ሽማግሎች ይገለገሉበታል ። በደስታ ጊዜ ህብረተሰቡ እዚህ ላይ ተሰብስቦ ይጨፍራል ። በኀዘን ወቅት ይረገድበታል ።

### ሠርግና ጋብቻ

በከምባታና ሃዲያ ብሔረሰቦች ዘንድ ሁለት ዓይነት የጋብቻ ዓይነቶች አሉ ። አንደኛው የቃል ኪዳን ማለትም ሽማግ

ወደ ገጽ ፰ ዞሯል



## ሙታን ድምፁን ይሰማሉ

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሁለተኛ መምጣት በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜያት በከፍተኛ ስሜት ለምእመናን ታስተምራለች የምታስተምርባቸውም ዕለታት አንደኛው በጌታችን በመድኃኒታችን ጾም እኩሌታ በሚውለው ደብረ ዘይት ተብሎ በሚጠራው ዕለተ ሰንበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘው ወርኃ ጳጉሜን ነው ።

በተጠቀሱት ወራት ክርስቶስ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚመጣ ታስተምራለች አንዳንድ አበው ሊቃውንት ደግሞ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት መታወስ ያለበት በአንድ ዓመት ውስጥ አራት ጊዜያት ነው፣ይሉና ለዚሁ ማስረጃ ሲያቀርቡ ቅዱስ ድሜጥሮስ ቀመረሐሳብ በፊት አንዱን አመት ቶቱ ወንጌላውያን 91 ቀን 91 ቀን እየተካፈሉ ይመግቡት ነበር የእያንዳንዱ ወንጌላዊ ድርሻም በተፈጸመ ጊዜ የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት ይታወስ ነበር ይኸውም አሁን እኛ በዓመቱ መጨረሻ በጳጉሜ እንደምናስታውሰው ማለት ነው ይሉና ቅዱስ ያሬድም ቢሆን ስለ ክርስቶስ መምጣት የዘመረው በሁለት ወራት ብቻ አይደለም በማለት ይናገራሉ ።

ያም ሆነ ይህ የክርስቶስን ሁለተኛ መምጣት የሰው ልጆች ሁሉ እንዳይዘነጉት እንዲያስታውሱት እስተውለውም ለመልካም ሥራ እንዲዘጋጁ እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም መቼም ቢሆን ክርስቶስ ሁለት ጊዜያት ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ቀደም ብሎ ተነግሯል አንደኛው ማለት በሥጋ የሚመጣበት አመጣጥ ተፈጽሞ ሁለተኛው በባሕርይ ክብሩ ዋጋ ለመክፈል የሚመጣበትን ፣ ሁላችን በተስፋ እንጠባበቃለን ።

የክርስቶስ የመጀመሪያ አመጣጡ ስለ ሰው ልጆች በደልና ኃጢአት ለመሞትና ሞቶም የሰውን ልጆች ከፍዳና ከመርገም ነፃ ለማድረግ ነበር እንግዲህ ወዲህ ግን ክርስቶስ ሁለተኛ ስለሰው ልጆች በደልና ኃጢአት ለመሰቀልና ለመሞት አይመጣም ሁለተኛ የሚመጣው መልካም ለሠሩ ሰዎች ዋጋቸውን መንግሥተ ሰማያትን ፣ ክፉ ሥራ ለሠሩ ደግሞ ፍዳቸውን ለመስጠት ነው ።

ክቡር ዳዊት ይህንን በመዝሙር ሲገልጽ" እግዚአብሔር ግልጽ ሆኖ ይመጣል አምላካችንም ዝም አይልም፣እሳት በፊቱ ይንቀለቀላል በዙሪያውም ብዙ አውሎ አለ በላይ ያለውን ሳማይን ምድርንም በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል" ብሏል መዝ 49 . 3 ።

የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሁለተኛ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ፍርድ መስጠት በቅዱሳት መጻሕፍት የተጻፈ ስለሆነ የሚያጠራጥር ባይሆንም የሚመጣበት ወርኅ ዘመን፣ዕለት ሰዓት ተለይቶ ሊታወቅ ከቶ አይችልም ። ደቀ መዛሙርቱ ሐዋርያት በጣም ቀራቢዎች እንደመሆናቸው መጠን አንድ ጊዜ ደብረ ዘይት በሚባለው ቦታ ብዙ ሕዝብን ሰብስቦ ስለ ሁለተኛ አመጣጡ ሲያስተምር ለብቻቸው ሆነው የሚመጣበት ወርኀ ዕለቱንና ሰዓቱን እንዲነግራቸው ጠይቀውት ነበር ክርስቶስ ግን የሚመጣበትን ወርኀ ዕለትና ሰዓት ወስኖና ቆርጦ አልነገራቸውም ።

ይሁን እንጂ የሚመጣበት ወራት በተቃረበ ጊዜ ከሚፈጸሙት ምልክቶች አልፎ አልፎ ነግሯቸዋል ፣ ክርስቶስ ለሐዋርያት ከነገራቸውም የምጽአት ምልክቶች ጥቂቶቹን እንመለከታቸዋለን ፣ "ብዙዎች እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና ብዙዎችንም ያስታሉ ጦርንም የጦርንም ወሬት ሰሙዘንድ ግድ አላችሁ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና ረኃብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል ከአመጽ ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች እስከ መጨረሻው የሚታገሥ ግን ይድናል" ካለ በኋላ "ስለዚያች ቀንና ሰዓት የሚያውቅ የለም" በማለት የደቀ መዛሙርቱን ጥያቄ ዘግቶታል ማቴ 24. 5 ፣ 12 - 26

ስለክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት የተነገሩት ምልክቶች ሲፈጸሙ ባየንና በሰማን ጊዜ ልናደርጋቸው የሚገቡትን ጥንቃቄዎች ራሱ ክርስቶስ ነግሮናል "ያን ግን እወቁ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍለ ሌሊት ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ በነቃ ቤቱንም ሊቆፍር ባልተወም ነበር ፤ ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ የሰው ልጅ በማታስቡት ሰዓት ይመጣልና ብሏል ማቴ 24.44

ለክርስቶስ ሁለትኛ መምጣት የሚያስፈልገው ዝግጅት በእግዚአብሔር ያለውን እምነት አጠንክሮ ፣ስነ ምግባርን አሳምሮ በሚገባ ተዘጋጅቶ መቀመጥ ነው ሰዎች ምጽዓቱን ዘንግተው ሃይማኖታቸውን አላልተው ምግባር ትሩፋታቸውን ርግፍ አድርገው ትተው በንዝህላልነት እንዳይኖሩ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በየጊዜው መልእክቷን ከማስተላለፍ አትቦዝንም ።

ክርስቶስ ሁለተኛ በመጣ ጊዜ ስለሚፈጸመው ድርጊት በማቴዎስ ወንጌል እንደሚከተለው ተጽፏል "የሰው ልጅ ወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ መላእክትን አስከትሎ በባሕርይ ክብሩ በመጣ ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል ፣ አሕዛብም በፊቱ ይሰበሰባሉ ንጉሥ ክርስቶስም ጻድቃንን ከኃጥአን ለይቶ ያቆማቸዋል" ይልና ፣

በመጀመሪያ ጻድቃንን እናንተ የአባቴ ወዳጆች ኑ ዓለም ሳይፈጠር ዘመን ሳይቆጠር የተዘጋጀላችሁን መንግሥተ ሰማያት ውረሱ በማለት በምድር በሠሩት መልካም ሥራ የማታልፈውን መንግሥተ ሰማያት ያወርሳቸዋል፣እን

ወደ ገጽ ፲፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የክብሩ ብርሃን ታላቅነት

## ከእጅጉ ረታ

ቤተ ክርስቲያን መታሰቢያነታቸውን በታላቅ ቁም ነገር ጠብቃ ከምታከብራቸው በዓላት አንዱ በዓለ ደብረ ታቦር ነው ። ይህ ዕለት በጌታ ምድራዊ ሕይወት ውስጥ ከፍተኛ ድርጊቶች ከተፈፀሙባቸው ዕለታት አንዱ በመሆኑ ፣ አበይት ተብለው ከሚጠሩት ከተሰዓቱ በዓላተ እግዚእ ውስጥ አንዱ ነው ።

ነሐሴ 13 ላይ ይውላል ። በመሠረቱ በዓላት የሚከበሩት የተፈጸሙ ድርጊቶችን መታሰቢያነት ለማስታወስ ነው ። ደብረ-ታቦር የሚለው ስም ፣ ግን ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቦታ ቢያመለክት እንጂ-ድርጊቱን ራሱን አያንፀባርቅም -የቦታ ስም ነው ። ጌታ ብርሃነ-መለኮቱን የገለጠበትን ይህን ዕለት ከእኛ በቀር ፣ ስሙን ደብረ ታቦር ብሎ - በቦታው ስም - የሚጠራው የለም ። በምስራቁም ሆነ በምዕራቡ የክርስትና ዓለም የሚታወቀው መለወጥ (ትራንስፊገሬሽን) ወይም በክብር መገለጥ ተብሎ ነው ።

ወንጌላውያን ስለ ጌታ ምድራዊ ሕይወት ባወሱበት ጊዜ ፣ ባጠቃላይ ክብደት የሰጡት ስለተፈጸሙት ድርጊቶች በመሆኑ ፣ ስለ ቦታ ስም እምብዛም የተጨነቁ አይመስልም ። ተራራ ፣ ከተማ ፣ ምድረበዳ እየተባሉ በወል በደፈናው የተጠሩ አያሌ ቦታዎች አሉ ። (ማቴ. 4. ቁ. 1 ። ማቴ 5 ፡ 1 ። ማቴ.14 ፡ 13 ማር. 1 ፡ 12 ። ማር. 3 ፡ 13 ። ሉቃ.6፡12 ። ሉቃ. 10፡38 ። ሉቃ. 11፡1) ወ.ዘ.ተ. ይሁን እንጂ ሥፍራዎቹ በዘመናት ጉዞ አልፈው ታሪካዊ መታሰቢያነታቸውን እንደያዙ እስከ ጊዜያችን ደርሰዋል ። ከእነዚህም አንዱ የታቦር ተራራ ነው የዚህ ተራራ ስም በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ውስጥ በውል ተለይቶ አልተመለከተም ። መድኃኒታችን በክብሩ ብርሃን ሲገለጥ በቦታው ተገኝተው የዐይን ምስክር ከነበሩት አንዱ ቅዱስ ጴጥሮስ "ቅዱስ ተራራ" አለ እንጂ ሌላ ስም አልጠራም ። (2ኛ ጴጥ. 1 18) ሌላው ደቀመዝሙር ደግሞ ፡- እርሱም ወንጌላዊ ዮሐንስ በጭራሽ ስሙን አላነሳውም ፡ ታሪኩን አላወሳውም ።

ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ታሪክ በመያዝ ግን ፣ የኦርቶዶክስና የላቲን አብያተ ክርስቲያናት ጌታ በባሕርየ መለኮቱ የተገለጠበት ቦታ የታቦር፡- ተራራ መሆኑን ያረጋግጣሉ ። በተራራው አናት ላይም አንድ ትልቅ የፍራንሲስካን ገዳም ለመታሰቢያ ተሠርቷል፡- መታሰቢያነቱም ከመካከል ያለው የጌታ ፣ በስተቀኝ ያለው የሙሴ ፣ በስተግራ ያለው የኤልያስ ነው ። አንድ መጠነኛ የሆነ የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም እንደዚሁ አለ ። የታቦር ተራራ 1.929 ጫማ ከፍታ ያለው ደን የለበሰ ውበትና ግርማን የተጐናፀፈ የደስ ደስ ያለው ተራራ ነው ፡- ከጥንት ጀምሮ ምናልባት በዚህ ጭምር ሳይሆን አይቀርም ቅዱስ ጴጥሮስ ነሽጦት በዚያ መኖርን ያስመኘው ። በሌላ አንፃር ጌታ ብርሃነ መለኮቱን የገለጠው በአርሞንኤም (ሔርሞን) ተራራ እንጂ ምን ቢያገድ በታቦር ይሆንና ያሉ አሉ። ለዚህ ያደረሳቸውም መድኃኒታችን ክብሩን ከመግለጡ ከስድስት ቀን በፊት ሰዎች ማን ይሉኛል ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን የጠየቃቸው በቂሣርያ ዘፊልጶስ ሳሉ ነበርና ፣ የአርሞንኤም ተራራም ከዚችው ከተማ 20 ኪሎ ሜትር ርቆ በስተሰሜን ሲል በመሆኑ ወደ "ረጅም ተራራ" ይዟቸው ወጣ የተባለለት አርሞንኤም ለማለት ነው ብለዋል።የአርሞንኤም ከፍታው 9.232 ጫማ የሆነ ጉግም ፣ በረዳም ተራራ ነው ። ለኑሮ የሚስማማ ፣ የሚያስመኝም አይደለም ። ቅዱስ ጴጥሮስም እንዲህ ያለውን ቦታ ለኑሮ የተመኘው አይመስልም ።

ብቻ ዋናው ቁም ነገር በብርሃነ መለኮቱ የመገለጡ ጉዳይ ስለሆነ ፣ ቦታው ያም ሆነ ይህ የሚያከራክር አይደለም ።

ጌታ የባሕርይ ክብሩ በሆነው በብርሃነ መለኮቱ የተገለጠው ያለ ምክንያት አልነበረም ። ይህ ከመሆኑ ከስድስት ቀን በፊት ከሐዋርያት ጋር በቂሣርያ ሳለ ፣ ስለእርሱ ማንነት ጠይቋቸው ሲመልሱለት አንዳንዶቹ ኤልያስ ፣ ሌሎቹም ከነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል ብለውት ነበር ። ስለዚህ እሱ ሙሴ ወይም ኤልያስ አለመሆኑን ተረድተው ጥርጣሬአቸውን እንዲያስወግዱ ሙሴና ኤልያስን ከእርሱ ጋር አምጥቶ አሳያቸው ። እንዲሁም በሙሴ ኦሪት ፣ በነቢያት መጻሕፍት ስለእርሱ የተጻፈው ሁሉ መድረሱን መፈፀሙን እንዲረዱት ለማድረግ ነው ።

የዓለም መድኃኒት በባህርይ ክብሩ በተገለጠ ጊዜ ሦስት ታላላቅ ነገሮች ተፈጽመዋል ። የመልኩ መለወጥ ፡ የሙሴና የኤልያስ ከእርሱ ጋር መታየት ፣ አብ ስለ ልጁ የሰጠው ምስክርነት ።

ፊት (ገጽ) አንድ ሰው ማንነቱ ተለይቶ የሚታወቅበት የሰውነት ዋና ክፍል ሲሆን፣ልብስም የአካል መሸፈኛ ነው ስለዚህ"...ፊቱም እንደፀሐይ በራ ፡ ልብሱም እንደብርሃን ነጭ ሆነ ተባለለት ። (ማቴ 17 2) ምሳሌው ወይም ማነጻጸሪያው ግን ፍጹም ፣ አይደለም ፤ ምሳሌ ዘየሐጽጽ ፡- መምሕራን እንደሚነግሩን ። መቼም ፀሐይ ብርሃኗ ዐይን ስለሚመዘምዝ (ስለሚበዘብዝ) ሙሉ በሙሉ ትክ ብሎ ሊያይዋት የማይቻል በመሆኑ ብቻ ፣ እናመሳስል ፣ እናነጻጽር ካልተባለ በስተቀር የፍጡር ብርሃን ከፈጣሪ ብርሃን ጋር በምንም ዓይነት ሊመሳሰል ሊነጻጸር እንዳይችል ግልጽ ነው ። ሙከራው የሰው አእምሮ ሊረዳው በሚችል ገንዘብ የተደረገ ማነጻጸሪያ እንጂ ፍጹምነት የለውም ። እንዲህ ነው ብሎ መግለጽ ያስቸግራል ።



ልዩ ብርሃን ነው፡- ለቅዱሳን በፀጋ ከሚሰጠውም ብርሃን የላቀ ነው ። ይህ ብርሃን ሙሴ ከሲና ተራራ ሲወርድ በፊቱ ላይ ከተሣለበት ብርሃንም ጋር ፈጽሞ አይመሳሰልም ፤ ልዩ ነው ። ሙሴ ፊቱን ሲሸፍን ልብሱ ብርሃኑ እንዳይታይ ፡ እንዲጋረድ ያደርገው ነበርና -የፀጋ ስለሆነ የበራውም ፊቱ ብቻ እንጂ መላ ሰውነቱ አልነበረም ። የዓለም ብርሃን ክርስቶስ ግን የተለወጠው ፣ ብርሃን የሆነው መላ-አካሉ፣መላ-ሰውነቱ እንጂ ፊቱ ብቻ አልነበረም ። በባሕርየ መለኮቱ ሲገለጥም ልብሱ ብርሃኑን ሰውሮ ሊያስቀረው አልቻለም።ልብሱ ራሱ እንደብርሃን ነጭ ሆነ እንጂ ። ይህ ብርሃን የክብሩ መንፀባረቅ ነውና (ልዩ ብርሃን) አማናዊ ብርሃን! መለኮታዊ ብርሃን !- -የብቻ ገንዘብ የሆነ እነሆ ይህ ፣ ብርሃን ፣ የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ ፊት ነው ። በተሣልቆ ምራቅ የተተፋበት ፣ በድፍረት በጥፊ የተመታውም ለዚህ በክብር ለተገለጠ ፣ ራሱን በገዛ ፈቃዱ ስለኛ በደል አሳልፎ በመስጠት ውርደትንና ሕማምን ለተቀበለ አምላክ ወዮ አንክሮ ይባላል ።

ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ ደመና ጌታ በክብር የመገለጡ ፣ በረድኤት የማደሩ ምልክት መሆኑን መጻሕፍት ተባብረው ገልጸዋል ። አባቶችን ያነጋግራቸው የነበረውም በደመና ሆኖ ነበር ። (ዘጸአት 19/9 ። 34/5 ። ዘኁልቁ 11 25 ዜና መዋ ካልዕ 5/13 - 14 ። መዝ 98 6 - 7 ሕዝ. 1/4 ወ.ዘ.ተ.) እንዲሁም ወልደ ዕጓለ እመሕያው ክርስቶስ በኃይልና በታላቅ ክብር ሁለተኛ የሚመጣው በብሩህ ደመና ነው ። (ማቴ 24/30 ራዕ1.7) (በታቦር ተራራ የባሕርይ ክብሩን ለመግለጥ በፈለገ ጊዜ ፣"ብሩህ ደመና ጋረዳቸው ፣ ከደመናውም ውስጥ ከእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው ፣ እርሱን ስሙት ፣ " የሚል ቃል መጣ ። ይህ ድምፅ በውሃ ተጠምቆ ሲወጣ በዮርዳኖስ የተነገረ ቃል (ድምፅ) ነበር።ለአጽንዖተ ነገር እዚህ ላይ ተደገመ ። ማቴ. 3/17 የተሰማው ድምፅ ቀድሞ ጌታ በሲና ተራራ ሕግን ለሙሴ ሲሰጥ መብረቅና ነጐድጓድ የተቀላቀለበትን መለከት የተሰማበትን የመሰለ አስፈሪ ፣ ወይም ኤልያስን በኮሬብ ተራራ በተነጋገረው ጊዜ አውሎ ንፋስ ተንጦ ምድር ተንቀጥቅጦ እንደተሰማው ያለ አሸባሪ ድምፅ አልነበረም ። ደስ የሚያሰኝ ውብ ድምፅ ፣ ልዩ ቃና ያለው ለስላሳ ፡- የምወደው ልጄ ይህ ነው ፣ እርሱን ስሙት የሚል ። እርሱን ስሙት ያለው ቃሉን ስሙት ሲለን ነው ፤ ቃል የተባለም ራሱ ከአብ ዘንድ የወጣው አንድ ልጁ ጌታ ክርስቶስ ስለሆነ የዘለዓለም ድኅነት ይሆንልን ዘንድ በእርሱ ማመን ዮሐ/14/24 ። እርሱን (ቃሉን) መስማት ነው ። ባጠቃላይ በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገረው ቃሉ የውነት ፣ የፍቅር ፣ የሰላም ፣ የደስታ ፣ የእረፍት ቃል ነው ። የመተሳሰብ የመረዳዳት ቃል ፡- የበጐነትን መንፈስ የተመላ ሕይወት የሚሰጥ እውነተኛ ቃል ነው ። (ዮሐ. 6/36) ልንሰማው ልንፈጽመው የሚገባ ነው።

እንግዲህ እነዚህ የፊተኞች (እሥራኤል ዘሥጋ) ሙሴ ይናገረን እንጂ እግዚአብሔር አይናገረን በማለት ከሚናገራቸው ከእርሱ በመራቃቸው ምክንያት ከቁጣው ካላመለጡ ፣ እኛም ከላይ ከመጣው ቃሉ (ከእርሱ) ፈቀቅ የምንል ከሆነ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን ? (ዕብ. 12 25)

ስለዚህ የሚፈርድብንም ይኸው ቃሉ እርሱ ስለሆነ (ዮሐ. 13/24) እምቢ እንዳንል እንጠንቀቅ ። ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውምና ። (ዮሐ. 3 17)

የጌታ የባሕርይ ክብሩ በታቦር ተራራ ላይ ብቻ ተገልጦ የሚቀር አይደለም እንዲሁም ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን ዋጋውን ለመክፈል በክብር በሥልጣን በጌትነትና በኃይል ዳግመኛ ይገለጣል ፤ ስለዚህ በክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ እንዳናፍር ለንስሐ የሚገባ ፍሬ ከአሁኑ ማድረግ አለብን ።



## ዜና ሊቃውንት....

ከገጽ ፲፮ የዞረ

### አማርኛ

የእሳት ነበልባል በነነዌ ሥላሴን አማችው ፣ የነነዌን ሥጋ ይመገብ ዘንድ ከሰማይ መቅደሱ ወርዶ ሆዱ እንደተራበ ሳይበላ ተመልሷልና ።

ነገር ግን እሱ የንጉሥ ኢያሱን ሥላሴን አይሟ በገሞራ በችግሩ ጊዜ በሆዱ ልክ የሰባ ሥጋን አጥግበውታልና ፣ የተረፈውንም ሎጥን አንሥተዋልና»

ሊቁ በቅኔ መዛግብት የተመዘገቡ ልዩ ልዩ ቅኔዎች ያሏቸው መሆናቸው ታውቋል ። ሕይወታቸውንም በዚህ ዓይነቱ ቁም ነገር ባለው ሁኔታ ሲመሩ ከኖሩ በኋላ የኢትዮጵያ ነጻነት እንደተመለሰ በ1934 ዓ.ም. አርፈው በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ ተቀብረዋል ።

ከአለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

www.ethiopianorthodox.org

# የሴቶች ዓምድ

አዘጋጅ ብርሃን ተድላ

## ቅድስት አትናስያ

አትናስያ ያዘኑትን የምታጽናና የተቸገሩትን የምትረዳ በጠቅላላ ምግባሯ የቀና ሥራዋ የፀና ርኅርኄትና ቸር ከመሆንዋም ሌላ በጥሩ ሥራዋ ያያት ሰው ሁሉ የሚወዳት በትሩፋቷ የምትደነቅ ቁመናዋና መልኳ ያማረ ልጃገረድ ነበረች ይላታል የቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ።

እንደዚህ ሁና ስትኖር መቸም ሰይጣን መጥፎ ነውና ይህንን ጥሩ ሥራዋን በማየት ቀንቶባት ሊያስስታት ፈለገ ። እርሷም በተለያዩ ነገሮች ቀስ በቀስ ስትታለል ቆይታ በመጨረሻ ከሰይጣን ወጥመድ ገብታ ንጽሕናዋንና ድንግልናዋን ትታ መልካም ሥራዋን ሁሉ እርግፍ አድርጋ ትጸየፈውና ትጠላው ወደ ነበረው ወደ ሴተኛ አዳሪነት ሥራ እንድትሠማራ አደረጋት።

በዚህን ጊዜ እርሷ ትረዳቸውና ታጽናናቸው የነበሩና መልካም ሥራዋን የሚያውቁ ሁሉ ወደዚህ አሳዛኝ ሥራ መሰማራቷን አይተው በጣም አዘኑ ። በመጨረሻም እነዚህ ምእመናን አውጥተው አውርደው ምን ብናደርግ ወደ ቀድሞው ሥራዋ ትመለስ ይሆን በማለት በመመካከር ዘዴ በመፈለግ በገዳም ወደሚኖር አንድ አባ ዮሐንስ ሐጺር ወደሚባል መነኩሴ ብንልክበትና እርሱ ቢመክራትና ቢገስጻት መልካም ሳይሆን አይቀርም ብለው በመወሰን እንዳሰቡት ወደእርሱ ሰው ላኩበት ።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም የአትናስያን ጥሩ ሥራ ቀደም ሲል ያውቅ ስለነበረ ሊመክራትና ሊያስተምራት ከገዳም ወደ ከተማ መጣ ። ከተማ ከመጣ በኋላም እርሷ ዘንድ ለመግባት የሚችልበትን ዘዴ በማጥናት ወደ አትናስያ ቤት አምርቶ ከቤቷ ደጃፍ ሲደርስ እመቤቴን ለማነጋገር እፈልግ ነበር ብትነግሩልኝ ብሎ ሠራተኞቿን ጠየቀ ።

ሠራተኛዋም እንግዳ ከውጭ መኖሩን ለመቤቷ ነግራ አትናስያም እንዲገባ ስለፈቀደችለት ሠራተኛዋ ሂዳ ይግቡ ተብለዋል በማለት መልስ ነገረችው ። እርሱም የገዳም ልብሱን ትቶ የከተማ ልብስ ለውጦ ከተሜ መስሎ ነበር የመጣውና ገባ እንደገባም ቁጭ እንዲል ጋበዘችው እርሱም ከፊት ለፊቷ ካለው መቀመጫ ሂዶ ቁጭ አለ ። እርሷ ግን ያው የተለመደው የከተማ ሰው የመጣ መስሏት ስለነበር አጠገቤ ናና እጫውተኝ እንጂ ለምን ርቀህ ተቀመጥክ ? ብላ ጠየቀችው ። እርሱ ግን በተቀመጠበት ቦታ ሆኖ እርሷን እያየ ያዝንና ያለቅስ ነበር ።

እርሷም በመደንገጥ ለምን ታለቅሳለህ ? ለምንስ ታዝናለህ ብላ ጠየቀችው እርሱም እኔማ የማለቅሰውና የማዝነው ውበትሽንና መልክሽን በማየቴ ነው አላት እርሷም ታዲያ የመልኬ ማማርና የውበቴ ማማር ያስደስታል እንጂ ያስለቅሳልን? ብላ ብትጠይቀው ምንም እንደዚህ ቢያምሩና ቢያጌጡ አንድ ቀን መፍረስ መበስበስ ስላለ ነዋ የሚያሳዝነኝና የሚያስለቅሰኝ አላት ይልና መጽሐፉ ጽሑፉን በመቀጠል ይህንን ሲነጋገሩ ልክ መብራት እንደበራባቸው እርግቦች ያሴስንዋት የነበሩት አጋንንት ሲወድቁባትና ሲነሱባት ይታየው ነበር እርሷ ግን አነጋገሩ በጣም ስለተሰማትና ስላሳዘናት በጠቅላላ መንፈሷን ባንድ ጊዜ ስለነካው ደከም ባለ ድምፅ ታዲያ ምን ባደርግ ይሻል ይመስልሃል? በማለት ትጠይቀዋለች ።

እርሱም ያለሽበትን የሴትኛ አዳሪነት ሥራ ትተሽ ተከተይኝ አላት እርሷም ያለ ሃብቷንና ንብረቷን ትታ ማቂን ጨርቄን ወርቄን ፣ ሃብቴን ሳትል ሌላው ቀርቶ እቤት ውስጥ የምታደርገውን ጫማ እንኳን ሳታደርግ በባዶ እግሯ በድንጋጤ ሮጥ ብሎ እንደሚወጣ ሰው ወጣ ብላ ተከትላው ሄደች ።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም ከፊት ከፊቷ እየመራ ሲሄድ እርሷ ትከተለው ነበር ከቤት ወጥታ የማታውቀው ወይዘሮ በጣም ረዥምና አድካሚ መንገድ ተጓዘች አፈር ረግጦ የማያውቀው እግሯ እሾህና እንቅፋት ተፈራረቁባት የውስጥ እግሯ ተላላጠ ቢቸግራት ነጠላዋን እየቀደደች ከሁለቱም እግሯ እስከታስር እንዳይሄድባት ቆየኝ መጣሁኝ ትለው ነበር እርሱም አይዞሽ ተከተይኝ እያለ መንገዱን ይቀጥላል ያሁሉ ስቃይና መከራ ግን እማሯት ወደ ደረጀውና ወደሞቀው ቤቷ አልተመለሰችም ወደፊት በምታገኘው ተስፋ በመጽናናት ከኋላ ከኋላው በመከተል መንገዷን ትቀጥል ነበር እንጂ ።

በመጨረሻም ከበአቱ ሲደርሱ አባ ዮሐንስ ሐጺር እሳት አንድዶ የምትመገበውን ሰጥቶ እርሷ ከዛ እንድታድር ነግሯት እርሱ ወደ ሌላ በአት ሄደ በዚህ

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል



# በመንፈስ ለሞቱ የትምህርት ትንሣኤ

በዚህ ዓለም ሁለት ዓይነት ምውታን አሉ አንደኛ የዚህን ዓለም ኑሮ ፈጽመው በሥጋ የሞቱ ሲሆኑ ፣ እነርሱም በመቃብር ውስጥ ሆነው የሕይወትን ትንሣኤ እስኪያገኙ ድረስ መናገር ማየት ፣ መስማት የሚደረገውን ነገር ሁሉ ማወቅ አይችሉም የደረቁ አጥንቶች ሆነዋልና ።

ሁለተኛ ደግሞ ትምህርትንና እውቀትን በማጣት በጨለማ ድንቁርና የተቀበሩ ፣ ብርሃኑ ጨለማ ፣ ጨለማው ብርሃን የሆነባቸው ፣ ሜዳው ገደል ፣ ገደሉ ሜዳ የሚመስላቸው ፣ ጣፋጩ መራራ፡ መራራው ጣፋጭ እየመሰላቸው የሚኖሩ ሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወታቸው የደረቀባቸው ምዕመናን ናቸው ።

ለምሳሌ በሾላ ውስጥ ያለ ትል እሱ ከሚኖርበት ከሾላ ቅርፊት ውስጥ በቀር ሌላ ዓለም ያለ ስለማይመስለው ደስ ብሎት ይኖራል የትምህርት ጸጋ የተገፈፈባቸው ፣ የእውቀት እድማስ የራቀባቸው ሰዎችም ከአካባቢያቸው በቀር ሌላ አዲስ ዓለም ሌላም የሥራ ሐገር ያለ አይመስላቸውም ስለዚህ እንዲህ ላሉት ሰዎች በትምህርት የዕውቀት ትንሣኤ ያሻቸዋል የመንፈስ ተሐድሶም ያስፈልጋቸዋል ምክንያቱም ትምህርት መንፈሳዊውን ነገር ለማወቅና ለመቀበል ወደ ሥራ ዓለምም ለመምራት የሚያስችል በመሆኑ ነው ። ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ ትምህርት የመልካም ነገሮች ምንጭ መሆኑን ሊቃውንት ራሳቸውን ጠቅመው ሌላውንም ጠቅመውበታል ።

ይህንንም የተገነዘበው ነቢዩ ሕዝቅኤል ከትምህርትና ከዕውቀት የእግዚአብሔር ቃል ከመስማት ተራቁተውና ተማርከው የነበሩትን እስራኤል በሙታን ፣ ባቢሎን በመቃብር ፣ ኑሮአቸውን በሸለቆ ሕይወታቸውን በደረቁ አጥንቶች መስሎ ትንቢት ሲናገር « እናንተ የደረቃችሁ አጥንቶች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል እነሆ ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንኩ ታውቃላችሁ » ብሏል ። ትንቢተ ሕዝቅኤል ምራፍ 37 ፣ 2 - 7

እንዳለውም እነዚህ አጥንቶች የወደቁበት ሥፍራ ሸለቆ እንደመሆኑ መጠን ውኃ የማይገኝበት የማይወርድበት ፣ ልምላሜ የማይታይበት ዝናብ የማያካፋበት ታላቅ በረሐ ስለ ነበረ በገዛ ጥረታቸው ሕይወትን ለማግኘት አልቻሉም። ሕዝቅኤል በሕይወት ትኖራላችሁ ያለው ስለዚህ ነበር ። በእርግጥም የተማረኩት ሕዝቦች በኃጢአት ጎስቁለው ስለነበር ብዙ ነገር ያስፈልጋቸዋል ። ይኸውም ሕይወት ስለሌላቸው አዲስ ሕይወት ፣ ትምህርት ፣ ንስሐ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት ሚጠት ፣ ነፃነት ያስፈልጋቸው ነበር ።

ሕዝቅኤል የተናገረው ለተማረኩት ቢሆንም ሁኔታው ተመሳሳይ በመሆኑ እኛም የምእመናንን መንፈሳዊ ሕይወት ለመቀስቀስ ነው የተነሳነው ለምሳሊ ሊቃውንት ትምህርት ሁለተኛ ፈጣሪ ነው ይላሉ በእርግጥም ሰውን ሥጋዊ ሕይወቱንም ሆነ መንፈሳዊ ሕይወቱን እንደገና ሊፈጥረው ፣ ሊያድሰው ሰው አድርጎ ከእውቀት ሊወልደው የሚችለው ትምህርት ነው ይህም አላማ ሊሳካ የሚችለው እንደ ሕዝቅኤል ያለ መልካም አስተማሪ ካህን ሲገኝ ነው እንዲህ ያለው ካህን በበምድረ በዳ የወደቁትን ማይማን በትምህርት ሊያስነሳቸውና ሕይወታቸውንም በእውቀት ሊያድስላቸው ይችላል በኃጢአት ሸለቆ ውስጥ ደርቆ የወደቀውንም የምዕመናን ሕይወት በንስሐ አድሶ በክርስቶስ ቃል ሕያው አድርጎ በመንፈስ ሙቀት ሰጥቶና አለምልሞ የመንፈሱ ፍሬ እንዲያፈራ ሊያደርግ ይችላል ።

ለምሳሌ ዶሮ ማርባት የምትወድ አንዲት ሴት ነበረች እርሷም ከሠላሳ የሚበልጡ እንቁላሎችን ሰብስባ ለብዙ ቀን አስቀመጠቻቸው እነሱም ሙቀት ከምትሰጣቸው እናታቸው ስለተለዩ በድን ከመሆን በቀር ሕይወትን አግኝተው ሊንቀሳቀሱና ጫጩት ሊሆኑ አልቻሉም ሴትየዋም ነገሩ እንዳልተሳካላት ባየች ጊዜ እንደገና ለእናታቸው አስታቀፈቻቸው እነሱም ሙቀት ስላገኙ ከሦስት ሣምንት በኋላ እንቁላሎቹ ወደ ጨጩትነት ተለውጠውና ሕይወት አግኝተው የእንቁላሉን ቅርፊት እናቲቱ ሰብራ አወጣቻቸው አድገውም ትልልቅ ዶሮዎች ሆኑላት ይህች ም ሴት ከመደሰቱዋም ሌላ በእግዚአብሔር ፍጥረት አፈጣጠርና ሕይወት ሰጪ መሆኑንም አደነቀች።

ምእመናንም እንደ ሕዝቅኤል ያለ ካህን የሚያስተምራቸው ካላገኙ ሕይወታቸው ይቀዘቅዛል መንፈሳቸውም በድን ይሆናል ተምረው ካወቁ ግን የመንፈስ ሙቀት የሚሰጣቸው እንደ ዶሮዋ ከክንፉ በታች የሚያቅፋቸው እናት አባት የሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስላላቸው የቀዘቀዘው ሕይወታቸው ይሞቅላቸዋል ።

እግዚአብሔር የሌለበት ሕይወት ግን መንፈሱ የቀዘቀዘ ነው በኑሮው ሰላም የለውም ሕይወቱ የደረቀ ነው ይህ ችግር ያጋጠመው ዳዊት በመዝሙር 37 ቁጥር 3 - 5 « ከኃጢአቴም የተነሣ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና እንደ ከባድ ሸክም በላይ ከብዶአልና » ብሏል ።

እንደተናገረውም ዳዊት ከባለጸግነት አልፎ ታላቅ መሪ ነበር ብዙ ምቾትም ነበረው የተመረጠ ምግብም ይመገብ ነበር ሙቀት የሚሰጥ ልብስም ይለብስ ነበር ። ይሁን እንጂ በዘመኑ የነበሩት ካህናት የሚሰራውን ኃጢአት እያዩ ስላላስተማሩትና ስላልገሰጹት መንፈሱ ቀዘቀዘ በዚህም የተነሳ ሰላም አልነበረውም አጥንቶቹም በኃጢአት ስለደረቁ ከመንፈስ ተራቁቶ ነበር ነገር ግን ነቢዩ ናታን በደለኛ መሆኑንና ንሥሐ እንዲገባ አስተማረው እሱም በኃጢአት የደረቁት አጥንቶቹ በመንፈስ እንዲለመልሙ ከእግ



www.ethiopianorthodox.org

ዚአብሔር ዘንድ ምሕረትን በመጠየቁ
የመንፈስ ተሐድሶን አገኘ ።

ይህ ከሆነ አልጫ የሆነውን የሰው ሕ
ይወት እንደ ጨው የሚያጣፍጡ ፣ እንደ
መቅረዝ ሆነው በጨለማ ውስጥ ላለው ብ
ርሃን የሚሰጡ፣የመንፈስ ንቃት እየሰጡ
በእውቀትና በትምህርት የሰውን አእም
ሮ እየገነቡ በንስሐ የሚያድሱ የደረቀ
ውን ሕይወት በክርስቶስ ቃል እንዲለ
መልምና የመንፈስ ፍሬ እንዲያፈራ የ
ሚያደርጉ እንደ ናታንና እንደ ሕዝቅኤል
ያሉ መምህራንን ቤተ ክርስቲያን በአሁ
ኑ ዘመን በመብራት ትፈልጋለች ።

ነገር ግን ቅዳሴ ከመቅደስ ሌላ ለስብ
ከተ ወንጌል ያልተዘጋጁ በቤተክርስቲ
ያን ትምህርት ያልሰለጠኑ ቅስናና ድቁ
ና የሚቀበሉ ካሕናት ሳያውቁና ሳይማሩ
በቤተ ክርስቲያን ሙያ ሳይሰለጥኑ ስር
ዓተ ምንኩስና የሚፈጽሙ ሁሉ ነቢዩ
ሕዝቅኤል በሸለቆ ወድቀው እንዳያቸው
አጥንቶች የደረቁ ስለሆኑ እንኳንስ ለሌ
ላው ሕይወትን መስጠታቸው ቀርቶ ለራ
ሳቸውም ሕይወትን የሚሰጣቸው የሚ
ፈልጉ በመሆናቸው የመንፈስ ትንሣኤ
ያሻቸዋል ማለት ነው ።

ይህንንም ለማወቅ ቢፈለግ በትግራይ
ሀገረ ስብከት ሰሚናር ካወጣው የጋራ
መግለጫ ጥቂቱን እንጠቅሳለን » ቅድ
ስት ቤተ ክርስቲያን ከመሥራችዋ
ከኢየሱስ የተሰጠ ሕግና መመሪያ ቢኖ
ራትም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ቋን
ቋዋን በማያውቁላትና ቋንቋቸውንም
በማታውቅላቸው ግብፃውያን አባቶች
አባቶች ሞግዚትነት ስትኖር ይደረግ
በነበረው የሥልጣነ ክህነት አሰጣጥ
ሥርዓት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት
ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ን ርስትና
የመከፈልትን ቅድሚያ ለመውሰድ ሲ
ባል በእናታቸው ጀርባ ባንቀልባ ታዝ
ለው ለሚቀርቡት ሕፃናት ማዕረገ ዲቁ
ና ሲሰጥ ተፈጥሮ ከሚያድላቸው ጉርም
ስና በቀር ምንም ዓይነት ትምህርት ሳይ
ጨምሩ የሥራ ሳይሆን የስም ቅስና ተብ
ቶብለው ይመለሱ እንደነበር አይዘነጋም።

አሁንም ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲ
ያን ጳጳሳትን የመሾም መብቷ ን ብትጨ
ብጥና ቃለ አዋዲም ብታወጣም በአፈ
ጻጸሙ ላይ ችግር ፈጥሮአል ። ድሮውንም
ካሕናቱ ተልእኳቸው ምን እንደሆነ አው
ቀው አልተሾሙምና ቅዱስ ሲኖዶስ ይ
ህን ቃለ አዋዲ ቢያወጣውም አበው ጳጳ
ሳት አሁንም ከግብፃውያን በወረሱት የ
ክሕነት አሰጣጥ ጉዳይ ስለቀጠሉበት
እስከ መቸውም ቢሆን ችግሩ የሚቃ
ለል ሆኖ አልተገኘም ።

ስለክህነት አሰጣጥ ክህነት መሰጠት
የሚገባው በትምህርቱ ብቃት በግብረ
ገብነቱ ፣ ቤተ ክርስቲያንን በትክክል የ
መምራት ችሎታው በምዕምናን የተመ
ሰከረለትና በምዕመናን የተመረጠ መሆን
እንዳለበት አያከራክርም ካለ በኋላ ሕጉን
የሚያስከብር አባል ባለመኖሩ ማንነታ
ቸው ያልታወቁ ወገኖች የዲቁናውንና
የቅስናውን ሥልጣን ተሸክመው ሲጓዙ
መታየታቸው አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑ ተ
ጠቁመዋል ።

ቀጥሎም ስለ ንስሐ አባቶች ባስተላለ
ፈው ውሳኔ በየመንግሥታዊ ድርጅቶች
ተቀብለው ከነሱ የሚያገኙትን ጥቅም
ብቻ በማሳደድ የቤተ ክርስቲያንን ሀል
ውና ስለሚዘነጉ ይህ የቤተ ክርስቲያን
መታደስ የእነሱን እንጀራ የሚዘጋባቸው
ስለሚመስላቸው ለሰበካ ጉባኤ መቋቋም
ታላቅ እንቅፋት ሆነው ተገኝተዋል ብሏ
ል ።

በእርግጥ የሕዝቡ አንገብጋቢ ጥያቄና
ለረጅም ጊዜ መፍትሔ እንደሚሆን አይ
ጠረጠርም ለምሳሌ ወጥ የሚጣፍጠው
በድስቱ ትልቅነት ፣ በመረቁ ብዛት ፣
የቅመሙ በገፍ መግባት ብቻ ሳይሆን
በሠራተኛዋ የሙያ አሰለጣጠን ነው በ
ቤተ ክርስቲያንም ስብከተ ወንጌል የሚ
ስፋፋው ፣ ምዕመናንም የመንፈስ ዕድ
ገት የሚያገኙት ሳይማሩ ዲቁናና ቅስና
በሚቀበሉ በካሕናት ብዛት ሣይሆን በተ
ማሩና በሰለጠኑ ጥራትና ዓይነት ባላቸው
ካህናት መሆኑ መታወቅ አለበት ።

የካህናትም ተልዕኮና አገልግሎት ቀ
ድሶ ማቁረብና ማጥመቅ ንስሐ አባትም
በመሆን ብቻ አይደለም አንድ ካህን ያነ
በበውን ምንባብ ትርጉመ ለሁሉ እንዲ
ገባው ማብራራትና በተጠየቀም ጊዜ መ
ልስ መስጠት የሚችል መሆን ይገባ
ዋል ካልሰበከ ፣ ካላስተማረ ግን የስም
ካህን እንጂ የሥራ ካህን ነው ማለት አይ
ቻልም ።

የሥራ ካህን ነው ለማለት የሚቻለው
በመንፈሳ የሞቱትን የትምህርትን የዕ
ውቀት ትንሣኤ አግኝተው እንዲነሱ የ
ሚያደርግ ፣ የደረቁ አጥንቶችን በክርስ
ቶስ ቃል የሚያለመልምና ወደ ሥራ ዓ
ለም የሚቀሰቅስ እንደ ሕዝቅኤል ያለ
ካህን በዘመናችን ቤተ ክርስቲያን ያገኘ
ችእንደሆነ ነው ምክንያቱም ዛሬ ሰዎች
ክርስቶስን ሊያዩት የሚችሉት በካህናት
ሕይወት አማካኝነት መሆኑን መዘንጋት
የለብንም ክርስቶስ ሲናገር « እኔ የዓለ
ም ብርሃን ነኝ » ብሏል ተከተዮቹንም
ደግሞ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ
ብሎአቸዋል ስለዚህ ካህናት ራሳቸው
ብርሃን ሆነው ሊላውን ብርሃን እንዲያ
ደርጉ ይፈለግባቸዋልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ



# ምን እንርዳዎ ?

ይህ ዓምድ አንባቢዎች ችግራቸውን የሚገልጹበት ፣ ለችግራቸው
መፍትሔ የ ሰጡበት ፣ ጥያቄና መልስ የሚያቀርቡበት ስለሆነ
ምን እንርዳዎ ተብሎ ተሰይሟል ።



አዘጋጅ ተስፋ ጥሩነህ
ስልክ ቍጥር 11-66-16
የፖ.ሣ.ቁ. 31-37
አዲስ አበባ

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሐዋር
ያዊ ድርጅት ምን እንርዳዎ አዘጋጅ
አዲስ አበባ

የጻድቁ የአቡነ ተክለሃይማኖት የሥራ
ተግባራቸው በመጽሐፈ ገድላቸው በግ
ዕዝ የተጻፈው በአማርኛ ተተርጉሞ የታ
ተመ ሲሆን ብዛቱ 253 ገጽ የያዘ በመሆኑ
ቅፁ ትልቅነት በኪስ ለመያዝ አያመችም
ስለዚህ 253 ቱን ገጽ በአጭሩ አውጣጥቼ
በ34 ገጽ አሳጥሬ የላክሁት ስለሆነ በመ
ጽሔት ታትሞ ለምዕመናን እንዲዳረስ
ይደረግ ዘንድ አሳስባለሁ ፣

«ኢትዮጵያ ትቅደም »
ግራዝማች በቀለ አሸብር
በሸዋ ክፍለ ሃገር በሰላሌ አውራጃ
በግራር ጃርሶ ወረዳ
በግሼ መረጨ ቀበሌ የገበሬዎች ማኅበር
ነዋሪ

ግራዝማች በቀለ ስለላኩልን ጽሑፍ
ከልብ እናመሰግናለን ። እርስዎ የላኩል
ን ብዛቱ 34 ገጽ ስለሆነ ብዛቱ በመጽ
ሔቱ ለማውጣት አላመቼም ስለዚህ በ
መጠኑም አጠር አድርገን የላኩልንን
ጽሑፍ በሚከተለው ሁኔታ አቅርበነዋ
ል።ጻድቁ ተክለ ሃይማኖት በሸዋ ክፍለ
ሀገር በመናገሻ አውራጃ በበረሀ ወረዳ
ልዩ ስሙ ፈጠጋር ኢትሳ እየተባለ
በሚጠራው ቦታ ከአባታቸው ከፀጋ ዘ
አብ ከእናታቸው ከእግዚእኃረያ ታህሣ
ሥ 24 ቀን 1197 ዓ.ም. ተወለዱ ። በተ
ወለዱ በ 40 ቀናቸው ሲጠመቁ ክር
ስትና ሲነሱ ስማቸው ፍሥሐ ጽዮን ተ
ብሎ ተሰየመ ። ዕድሜያቸው ለትምህ
ርት ሲደርስም ካባታቸው እየተማሩ መዝ
ሙረ ዳዊት ድረስ አውቀዋል ። ከዚያም
ብሉያትና ሐዲሳትን ፣ እንዲሁም ሕገ
ቤተ ክርስቲያንንና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲ
ያንን አጠናቀው አውቀዋል ። በትምህ
ርታቸው ጊዜ ትምህርታቸውን መንፈስ
ቅዱስ ስለሚገልጽላቸው አይቸገሩም
ነበር ጻድቁ ፍሥሐ ጽዮን ከትህትናቸው
ከጠባያቸው ከቁም ነገራቸው የተነሣ
ያያቸውና ዝናቸውንም የሰማ ሁሉ ይወ
ዳቸውና ያደንቃቸው ጀመር ።

ፍስሐ ጽዮን ገና ከልጅነታቸው ጀም
ረው ጾምና ጸሎት አዘወተሩ ። እጅግ ት
ዕግስትኛ ሆኑ ፍስሐ ጽዮን 17 ዓመት
ሲሆናቸው ዲቁና ይቀበሉ ዘንድ አባታ
ቸው ፀጋ ዘአብ ወደ ጳጳሱ ወደ አባ ጊር
ሎስ ወሰዱዋቸው ። እነርሱ ወደ አባ ጊ
ርሎስ ከመድረሳቸው በፊት የእግዚአብ
ሔር መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ለአባ ጊር
ሎስ ተገልጸ "ነገ ወደ አንተ አንድ ልጅ
የያዘ ሰው ይመጣል ። ሕፃኑ በእግዚአብ
ሔር ዘንድ የከበረ ነው ። ስለዚህም ፈጥ
ነህ ዲቁና ሹመው በፍቅር ተቀብለህ በ
ፍቅር ሸኘው ብሏቸው መልአኩ ተሠ
ወረ ።

አባ ጌርሎስም ይህን የቅዱስ ሚካኤ
ልን ንግግር ሰምተው ሌሊቱን ሁሉ ሲያ
ደንቁ አደሩ ። በማግስቱም በመልአኩ
ቃል መሠረት አባ ጌርሎስ ከክህነት መ
ስጫው አደባባይ ከክብር ቦታቸው እንደ
ተቀመጡ ካህናቱ ዙሪያውን ተሰበሰቡ።

በዚህ ጊዜም ፀጋ ዘአብም አብሮ ቀረበ
አባ ጌርሎስ መልአኩ በነገራቸው የመ
ልክ ምልክት ፀጋ ዘአብን ስለአወቁት
ፀጋ ዘአብን አስጠርተው ልጅህ የት አለ?
በእግዚአብሔርና በመላእክት ዘንድ የከ
በረ ነውና ። ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር
ለወገንም ሞገስ ነው ብለው ሲናገሩ ፀጋ
ዘአብ ተደንቆ ዝም ብሎ ቆመ፣አባጌር
ሎስም ልጅህ የት አለ ? ነው የምልህ ሲ
ሉት አለ የሚል መልስ ሰጠ ፈጥነህ አም
ጣው እግዚአብሔር እንዳከበረው እኔም
እንዳከብረው ዳሩ ግን እግዚአብሔር አከ
ብሮታልና እኔ ላከብረው አልችልም ።
ብቻ እኔ ኃጥእ በእሱ ክብር እከብር ዘን
ድ አከብረዋለሁ ።

አባ ጊርሎስ ይህንን ሲናገሩ ፀጋ ዘአብ
ፍስሐ ጽዮንን ወደ ጳጳሱ አቀረባቸው።
አባ ጊርሎስም ፍስሐ ጽዮንን ባዩ ጊዜ
ከመቀመጫቸው ተነስተው አቅፈው ሳ
ሙዋቸው። ሕዝቡም ጳጳሱ ተነስተው ሕ
ፃኑን ሲስሙ አይተው ደነገጡ ። ከዚህም
የተነሣ ሕዝቡ ለዚህ ሕፃን የተነሣኸው.
ስለምንድር? ነው ብለው ጠየቋቸው አባ
ጌርሎስም ስለዚህ ሕፃን ክብር እኔ ያወቅ
ሁትን እናንተ አላወቃችሁትም አሏቸ
ው ። ይህ ልጅ በጌታችን በኢየሱስ ክር
ስቶስ ዘንድ እንዲሁም በእናቱ በቅድስት
ድንግል ማርያም ዘንድ የከበረ ነው ። አ
ሁንም ብቻውን አይሄድም ቅዱስ ሚካ
ኤል የእሳት ሰይፍ ይዞ ይከተለዋል።ከዚ
ህ በኋላ ፍስሐ ጽዮንን ከአጠገባቸው አ
ሳድረው በማግስቱ ቀድሰው ፍሥሐ
ጽዮንን ሲመተ ዲቁና ሰጧቸው ። ከዚ
ህ በኋላ ፍሥሐ ጽዮንንና አባታቸውንም
ሶስት ሱባኤ 21 ቀን ከእርሳቸው ጋር
እንዲቆዩ አደረጉ በመጨረሻም ወዳገ
ራቸው ሸኙዋቸው ። ፍሥሐ ጽዮን በመ
ንፈሳዊ ሥርዓት ጎለመሱ፣በሥጋም አደ
ጉ ከዚህ በኋላ ለአካለ መጠን ስለደረሱ



www.ethiopianorthodox.org

# ዜና ሊቃውንት

## አለቃ እንግዳ ደስታ

በታሪክ የታወቁት አለቃ እንግዳ ደስታ ከስመ ጥሩውና ከባለሙያው አባታቸው ከመልአከ ፀሐይ ደስታና ከእናታቸው ከወይዘሮ አበባ ገብረማርያም በአሥራ ስምንተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ በዓፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግሥት በጎንደር በአጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል አካባቢ ተወለዱ ።

የመጀመሪያውን ደረጃ የንባብ ትምህርት በአጠቃላይ ፀዋትወ ዜማን አቋቋም ጭምር በጎንደር ከተማ ካጠናከሩ በኋላ በጎጃም ክፍለ ሀገር ውስጥ ወደሚገኘው ወደ ዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ተዛውረው ከመምህር ተጠምቆ ቅኔ ከነ አገባቡ ተምረዋል ።

ከትምህርት ዓለም ተላልፈው የማስተማር ችሎታ ማረጋገጫ የሆነውን ምርቃት በተቀበሉበት በዚሁ በቅኔ ሞያቸው ታሪካዊ ዝና ማትረፋቸውና ፍሬያማ ውጤት ማስገኘታቸው የታሪክ ሐቅ ነው፣ ይኸውም በገዳማትና በአድባራት እንዲሁም በታወቁ ታላላቅ ሰዎችና ሊቃውንት ዘንድ ያበረከቱዋቸው ቅኔዎች ለቅኔ ፈጠራ ችሎታቸው መረጃዎች ስለሚሆኑ ነው ።

በተጨማሪም በሥነ ጽሑፍ ረገድ ብሔራዊ የሆነውን ቀይና ጥቁር ቀለም ከልዩ ልዩ ፍሬያትና ዕፅዋት ቀምመው የሸንበቆ ብዕር ቀርፀው ከፍየልና ከበግ ቆዳ ብራና ፋቀው ፣ ቅዕ አውጥተውና ከፍፈው በቁም ጽሕፈት የጻፏቸው የንባብ፣ የዜማ፣ የትርጓሜ መጻሕፍት፣ የኪነ ጥበብ ሰው መሆናቸውን ያረጋግጣሉ።

ከዜማና ከቅኔ እንዲሁም ከቁም ጽሕፈት ሞያቸው በላይ ትርጓሜ ሐዲሳትን በሚገባ የተማሩ በመሆናቸው የሊቃውንቱን ስመ አጠራር መድረክ ሊረከቡ ችለዋል ማለት ሊቁ አለቃ እንግዳ ደስታ ለመባል በቅተዋል ።

አለቃ እንግዳ የሊቅነታቸው የሞያ ምጥቀትና ጥልቀት በአገር ውስጥ ትምህርት ብቻ ተወስና እንዲቀር ባለመፍቀዳቸውና አርቀው በማሰባቸው ከኢትዮጵያ ውጭ ወደሆኑ አገሮች ሔደው የልዩ ልዩ የቋንቋ ትምህርት ለመከታተልና የምርምር ተቅዋማቸውን ለማጠናከር ያልተገታና ጊዜ ያልወሰነው ፍላጎት ነበራቸው ።

ተግባራዊ የሚሆንበትን ወቅት በመጠባበቅ ላይ ሳሉም የጎንደር ከተማ በድርቡሾች እጅ መውደቅና መጥፋት ትኩስ አሳባቸውን በሥራ ለመተርጎም አጋጣሚ ሆናቸው ።

አለቃ ደስታ በልዩ ልዩ ባሕላዊ ቅርስና ታይተው ተጠይቀው በማይጠገቡ ሊቃውንት እብባ የነበረችው ጎንደር በደርቡሾች በመመዝበሯና ሊቃውንቷን፣ መጻሕፍቷን በማጣቷ ከፍ ያለ ኀዘን ስለተሰማቸው ይህ የመከራ ጊዜ ከትውልድ አገራቸው ከጎንደር የሚወጡበትና ለትምህርት የውጭ አገር ጉዞዋቸውን አቅጣጫ የሚቀይሱበት ጊዜ መሆኑ በትክክል ታወቃቸው ።

በዚህ ምክንያት የትራንስፖርት ይዞታ እጅግ ከባድና አስቸጋሪ በነበረበት በዚያን ጊዜ ከኢትዮጵያ በስደት ወደ እንግሊዝ አገር ሔደው የእንግሊዝኛ ትምህርታቸውን በአንዳንድ የምርምር ይዘት ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አካባቢ የሚያፈነግጠውን የሳይንስ ትምህርት በሚገባ አድርገው እየተከታተሉ ገና በአገራቸው ሳሉ የተማሩዋቸውን የቅዱሳት መጻሕፍት ስልትና ምሥጢር ከመጽሐፍቅዱስ በማስተያየት ፣ ከአውሮጳም ሊቃውንት ቃል በቃል መነጋገር መከራከር ጀመሩ።

የትምህርትና የምርምር ይዞታቸውን ለሐያ አራት ዓመታት ያህል በእንግሊዝ ዋና ከተማ በለንደን ሲያጠናክሩ ከኖሩ በኋላ በትምህርትና በምርምር ያጠናከሩትን ሞያ ለኢትዮጵያዊት አገራቸውና ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው ለማትረፍ በ 1903 ዓ .ም አካባቢ ወደትውልድና ወደ ትምህርት አገራቸው ወደ ጎንደር ተመለሱ ።

በጊዜው ጎንደርን ያስተዳደሩ የነበሩት ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ የሊቁን ሙያና ሁኔታ ቀደም ብለው ተገንዝበውት ስለነበር በመጀመሪያ የቅዱስ ፋሲለደስን ቀጥሎም የአጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤልን አድባራት በየተራ ሾመው እያስተማሩና መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን እያበረከቱ በክብር እንዲኖሩ አድርገዋል ።

ሊቁ በዚህ ዓይነቱ ይዞታ ላይ ሳሉም ንጉሥ ወልደ ጊዮርጊስ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ በተማረና በተመራመረ ሊቅ ላይ ትኩረት የሚያደርጉት ታላቁ ሊቅ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ዝናቸውን ቀደም ብለው አጥንተውት ኖሮ ከመንግሥት አስፈቅደው ከጎንደር ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡና በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሠሩ አደረጉ ።

ሊቁም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በቋሚ ሠራተኛነት ከተመደቡ በኋላ የውጭ አገሮች ቋንቋ ትርጉም ባለሙያዎች እጥረት በነበረበት በዚያን ጊዜ ልዩ ልዩ የሆኑ ጽሑፎችን ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ ፣ እንዲሁም ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም የምርምር በር በመክፈትና በማስረዳት አገሩን ወዳድ ከሆነ ኢትዮጵያዊ የሚጠበቅ ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክታዋል ። እንግሊዝኛ በማስተርጎማቸውም አፈንዲ ዳንኤል ተብለዋል ።

ሊቁ የቅኔ ባለሙያ መሆናቸውን ከላይ አመልክተናል ስለዚህም ለመረጃ ያህል ተቀኝተውት የነበረውን ሥላሴ ቅኔ በግእዝና በአማርኛ ከዚህ በታች ገልጠነዋል ።

“ሐመዮሙ በነነዌ በልባሰ እሳት ለሥላሴ ፣ ሥጋ ነነዌ ይሴሰይ ወሪዶ እምነሰማይ መቅደሱ ።
እስመ ገብዓ እንበለ በሊዕ ከመ ርኅበት ነፍሱ
ባሕቱ ኢይህሚ ለሊሁ አጋዕዝተ ንጉሥ ኢያሱ
እስመ በገሞራ ጊዜ ትዕናሱ
አጽገብዎ ሥጋ ሥቡሐ መጠነ ከርሡ ወሎጥሃ ዘተርፈ እግኃሡ ።”

ወደ ገጽ ፱ ዞሯል



# ከቤተክርስቲያን የታሪክ ዐምድ

## መስከረም 1973 ዓ.ም.

1ኛ የ1973 ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀ መንበር ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ቡራኬና መንፈሳዊ መልእክት በራዲዮና በቴሌቪዥን አስተላልፈዋል ።

2ኛ መስከረም 16 ቀን 73 ዓ.ም. በዓለ መስቀልን ከብፁዓን ጳጳሳትና በብዙ ሺህ ከሚቆጠሩ ምእመናን ጋር አክብረዋል ቅዱስነታቸው በበዓሉ ላይ ለተገኙት ምእመናን ነገረ መስቀሉን አስመልክተው ቃለ ምእዳን አሰምተዋል ።

## ጥቅምት

3ኛ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሊቀ መንበርነት የሚመራው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ከጥቅምት 12-29 ቀን 1973 ዓ.ም. በምልዓተ ጉባኤ ተሰብስቦ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደርና መንፈሳውያን ጉዳዮች በመወያየት ውሳኔዎችን አስተላልፎአል ።

4ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ አዲስ በመሠራት ላይ የነበረውን የቦሌ ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤልን ሕንፃ ጥቅምት 9 ቀን 73 ዓ.ም. ጐብኝተው መንፈሳዊ ምክርና መመሪያ ከሰጡ በኋላ ቀደም ሲል መልካም አገልግሎት ላበረከቱ ካህናትና የሰበካ ጉባኤ አባላት የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ።

ከዚህም ሌላ ቅዱስነታቸው በአሥመራ ከተማ በሰሜናዊ እዝ ሆስፒታል አካባቢ ለሚገኘውና በመሠራት ላይ ለነበረው የደብረ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያ አሥር ሺህ ብርና ለቤተ ክስስቲያኑ መገልገያ ንዋያተ ቅድሳት ሰጥተዋል ።

## ኅዳር

5ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ኅዳር 11 እና 12/73 ዓ.ም. በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በደብረ ብርሃን ከተማና በአንኮበር ወረዳ ተገኝተው በዚያ የሚገኙትን ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል ።

6ኛ ቅዱስነታቸው ኅዳር 21 ቀን በየዓመቱ የሚከበረውን የእመቤታችን በዓል በኅሐ ጽዮን ተገኝተው አክብረዋል ወዲያውም ጥንታዊትዋን የኅሐ ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ጐብኝተዋል ።

7ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ኅዳር 26 ቀን 73 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕፃናት ተወካዮችን ተቀብለው አነጋግረዋል ። ቅዱስነታቸው ተወካዮችን ካነጋገሩ በኋላ ለሕፃናት ኮሚሽን መርጃ የሚሆን አሥር ሺህ ብር ሰጥተዋል ።

## ታኅሣሥ

8ኛ ታኅሣሥ 19 ቀን 73 ዓ.ም. በቁልቢ ተገኝተው የመልአኩ ቅዱስገብርኤልን በዓል ከማክበራቸውም በላይ በሐረርና በድሬዳዋ ከተማ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል።

9ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ታኅሣሥ 28 ቀን 73 ዓ.ም. ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በራዲዮና በቴሌቪዥን ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል ።

10ኛ ታኅሣሥ 28 ቀን እና 29ቀን 73 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ የሚገኙትንና ንጉሥ ላሊበላ ያነፃቸውን አሥር ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል ። ቅዱስነታቸው ገዳማቱን በጐበኙበት ወቅት በአካባቢው ለሚገኙት ካህናት የገንዘብ ስጦታ ከማድረጋቸውም በላይ በዚያ ለሚኖሩት ካህናት መተዳደሪያ የሚሆን የጎጆ እንዱስትሪ እንዲቋቋም ተስፋ ሰጥተዋል ።

በዚያው ዕለት ቅዱስነታቸው በላሊበላ አዲስ የተቋቋመውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የሕፃናት ማሳደጊያ ድርጅትን መርቀው ከፍተዋል ።

11ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ታኅሣሥ 25 ቀን 1973 ዓ.ም. በሐይቆችና ቡታ ጅራ አውራጃ በዝዋይ የካህናት ማሠልጠኛ ተገኝተው ማሠልጠኛው ለ5ኛ ጊዜ ለአሠለጠናቸው ካህናት የምስክር ወረቀት ሰጥተዋል ።

## ጥር

ጥር 11 ቀን 1973 ዓ.ም. የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገኙበት በአ.አ. ከተማ ከፍተኛ ድምቀትና በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ተከብሮአል ።

12ኛ ጥር 24 ቀን 1973 ዓ.ም. የክርስቲያን አንድነት የጸሎት ቀን አዲስ አበባ በሚገኘው መንበረ ሀባየት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ተከብሮአል ። በበዓሉም ሥነ ሥርዓት ላይ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የተላከ መንፈሳዊ መልእክት ተነብቦአል ። የቅዱስነታቸውን መልእክት በንባብ ያሰሙት ብፁዕ አቡነ ገብርኤል ናቸው ። እንዲሁም ከጥር 20 - 27 ቀን 1973 ዓ.ም. በአሥመራ ከተማ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተው መንፈሳዊ መመሪያ ሰጥተዋል ።

## የካቲት

13ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከየካቲት 3-9 ቀን 1973 ዓ.



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

## ሃያ አምስት እድሜ ያለው ጋብቻ

በማንኛውም የዓለም ኅብረተሰብ እ ያንዳንዱ መንግሥት ወይም ሕዝብ የብ ዙ ቤተሰብ ድምር ነው ይህም በጥንታ ዊው የተፈጥሮ ሕግና ትእዛዝ

- ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት

- ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከ ሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አን ድ ሥጋ ይሆናሉ በሚል ቃለ በረከት የተቀደሰ ሥርዓት ነው ። ክርስቶስም በሐዲስ ኪዳን«እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው መለየት አይችልም » በሚል መለኮታዊ ቃል አጽንቶት እናገ ኛለን ። ማቴ 19 ቁ 3 ይህንም ሁሉ መሠ ረት በማድረግ ደቀ መዛሙ ርቱ የጋብቻ ን ቅድስና በመግለጥ ሲናገሩ - ጋብቻ በ ሁሉ ዘንድ የከበረ ይሁን ዕብ 13 ቁ 3

-ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ ወደደ እናንተም ባሎች ሚስቶቻችሁን ውደዱ ኤፌ 5 ቁ 21 - 33 በሚል ኃይለ ቃል ተጽፎአል ።

በዚህ አንጻር ደግሞ የጋብቻ መፍረስ የሕብረተሰብ መቅሰፍት ሆኖ ብዙ ልጆ ችን ያለ እናትና አባት ማስቀረቱ ይታ ያል ፣ ይህም በወንጌል ሕግ የተከለከለ መሆኑን በመገንዘብ በማቴ 5 ቁ 32 እኔ እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስ ቱን የፈታ አመንዝራ ያደርጋታል ። የተ ፈታችውንም ያገባ ያመነዝራል ። ካለ በኋላ በዚሁ ምዕራፍ ከፍ ብሎ « ሙሴ የፍችዋን ምክንያት በደብዳቤ ሰጥቶ ማ ሰናበት እንደሚችል የጻፈበት ምክን ያት ምንድነው ሲሉ ፈሪሳውያን ላቀረ ቡት ጥያቄ ሲመልስ ሙሴ ይህንን የፈ ቀደበትን ምክንያት ስለ ልባቸው ደንዳናነ ት ነው በማለት የማያዳግም መልስን



አቶ ፋንታዬና ወ ሮ እጅግአየሁ ፳፭ኛ ዓመት የጋብቻ በዓላቸውን ሲያከብሩ

ሰጥቶ የመፍታትን ዝንባሌ ክርስቶስ እ ንዲገታ አድርጓል ።

ስለዚህም ይህን ዓይነት ክርስቲያናዊ ሥርዓት በመከተል ቅዱስ ጋብቻንመሥ ርተው የጋብቻ ቸውን ሃያ አምስተኛ ዓ መት ያከበሩትን አቶ ፋንታዬ ይመርና ወ እጅግአየሁ ሰይፉን አነጋግረናል።

አቶ ፋንታዬ ይመርና ወ ሮ እጅግ አየሁ ሰይፉ ዕድሜአቸው ለአቅመ አዳ ምና ለአቅመ ሔዋን ሲደርስ ማለትም የሃያ አንድ ዓመት ጎልማሳ በነበሩበት ጊዜ የአስራ አምስት ዓመት ዕድሜ ከነ በራቸው ወ ሮ እጅግአየሁ ጋር በሀገራ ችን ወግና ሥርዓት መሠረት ሰኔ 3 ቀን 1948 ዓ.ም.ጋብቻቸውን እንደመሰረቱ ነግረውናል ።

አቶ ፋንታዬ ይላሉ በዚህ የጋብቻ ዘ መናችን ውስጥ በኑሮአችን ሁሉ ከቤተ ሰቦቻችን ጋር የምናደርገው አካሄድ ፍ ቅርና ሰላም የመላበት በመሆኑ የምንደ ሰትበት አንደኛውን መልካም ነው ብለን የምንቆጥረው ይኸ ሲሆን በዚህ የጋብቻ ዘመናችን የወለድናቸው አሥራ አንድ ልጆች አሉን ።

ከነዚህ ውስጥ አፏን ካልፈታችው የስ ምንት ወሯ ሕጻን ልጃችን በስተቀር ሁ ሉም ፈሪሀ እግዚአብሔር ያደረባቸው ፣ ወላጆቻቸውን የሚያከብሩና የሚታዘ ዙ በመሆናቸው የሚሰማን የመንፈስ ስታ ከሁሉም ነገር ይልቅ ታላቅ ነው።

ለቤተሰቦቻችው ያለባቸው ሃላፊነትና ድርሻም ምን እንደሆነም ጠይቀናቸው ነበር ልጆቻችን በሥጋዊና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በምግባርና በሃይማኖት የተስተካከሉ ሆነው እንዲያድጉልን ባ ለን አቅማችን ሁሉ የምናደርገው ጥረት ይኸ ነው አይባልም እኔ ከውጭ ሠርቼ ሳመጣ እሷ ደግሞ ከቤት ልጆቻችንን በመጠበቅና ቤታችንን በማዘጋጀት ለም ንኖርበት ኑሮአችን በአንድነት እየተጋገን ለቤተሰቦቻችን የሚኖርብንን ሃላፊነትና ድርሻ እንዳይጎድልባቸው ማድረግበሥ ጋዊ ሕይወት ለሚኖርበት ኑሮ መልካም አስተዳደግን አትርፈው በትምህርት ታ ንፀው እንዲያድጉልን ሃላፊነታችንና ግ ዴታችን መሆኑን እናምናለንና ጥረታች ን ብዙ ነው።ወ ሮ እጅጋየሁም በዚሁላይ ሲያክሉበት አሁንም በምናየው የልጆ ቻችን ፀባይ እጅግ ነው የምንደሰተው ዘለቄታቸውም በዚሁ እንደሚሰምር ተ ስፋ አለን ልጅን በሚሄድበት መንገድ



ምራው በሸመገለም ጊዜ ከርሱ ፈቀቅ አይልም በሚለው አምላካዊ ቃልመሠረት የአሁኑ አስተዳደጋቸው ለወደፊቱም መመሪያቸው እንደሆነ እናውቃለን ። አሁንም በቤተሰቦቻቸው መካከል ሲሆኑ የሚሰማቸው ምን እንደሆነ ለጠየቅናቸ ው ሲመልሱም ።

ገልፀው ላልፍ የማልፈልገው ሲሆን ለሌ ሎች ባለትዳሮች የማስተላልፈው ቢኖር ብቸኛ ከሚሆኑ ይልቅ የተቀደሰ ጋብቻ መሥርተው በቤተሰብ መካከል የኖሩ እንደሆነ በሕይወታቸው ሊያደርጉት ከ ሚገባቸው ዋና ዋና ነገሮች አንደኛውንና ትልቁን ድርሻቸውን ተወጥተውታል



የ፳፭ ዓመት ቅዱስ ጋብቻ ያስገኛቸው ፲፩ ፍሬዎች

የአምላክ እጅ ሥራ የሆኑትን የልጆችን በረከት ማግኘት ትልቅ ፀጋ ነው ። በል ጆቼ ያለኝ የአሁን ደስታና የወደፊትም ተስፋ የላቀ ነው ሲሉ አቶ ፋንታዬ ወ ሮ እጅግአየሁም ቀጠል በማድረግ ወ ላጆቼ ብዙ ልጆች ስላልወለዱ በቤተሰብ መካከል አላደኩምና በዚሁ ሁኔታ የሚ ኖሩትን ሳይእንን ነበር አሁን ግን እግዚ አብሔር ክብርና ምስጋና ይድረሰውና እመኘው በነበረ የቤተሰብ ሁኔታ ውስጥ ስለሚኖረኝ እደሰታለሁ ። በልዑል መጠ ጊያ የሚኖር ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላው ውስጥ ያድራል ። መዝ 90 91 በመጨረሻም ወ ሮ እጅግአየሁ የሚሰጡ ን አጠቃላይ ሃሳብ እንዳላቸው ለጠየቅ ናቸው ሲመልሱ እነዚህን ሁሉ ልጆች በምወልድበት ጊዜ ባለቤቴ አንድ ቀን እንኳ ተበሳጭቶ አያውቅም ይልቁም በፀነስኩኝ ቁጥር የሚያደርግልኝ እንክ ብካቤ ሁሉ እንደመጀመሪያ ወላድ ስለ ማይለየኝ እኔም እነዚህን ሁሉ ስወልድ ምንም ችግር አልተሰማኝም ። ይኸ ሳል ማለት ይቻላል ብለዋል ።

አቶ ፋንታዬንም ማጠቃለያ ሃሳባቸ ን እንዲሰጡን ለጠየቅናቸው እንዲህ ይላሉ እኔ የምሰጠውን ሃሳብ በጣም በሚገርመኝ እጀምራለሁ ይኸውም አን ዳንድ ሰዎች እነ እከሌ ብዙ ልጆች አላ ቸው ማለትን ሲሰሙ እግዜር - ያሳድግ ላቸው በማለት ፋንታ እነሱስ አበዙት አይሰለቻቸውም እንዴ ይላሉ የዛሬሃያ አምስት ዓመት በሠርጋችን ዕለት የነበ ረውን አንድ ጓደኛዬ እንደገና ብዙ ዓመ ት ቆይተን ስንገናኝ ከሰላምታው ቀጥሎ አሁንም ከዚያችው ባለቤትህ ጋር ነህ እንዴ ብሎ ጠየቀኝ ፣ እኔም እንዴታ አ ልኩት ምን ዓይነት ሰው ነህ እባክህ ከአ ንድ ሴት ጋር መኖር አይሰለችህም እንዴ ያለኝን አልረሳውም እኔም በነገሩ በጣም አዘነኝ አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ በሚ ለው የእግዚአብሒር ቃል ፀንቼ እኖራ ለሁ አንተ ግን ሁሉ ቤቴ ፣ ሁሉ ሚስቴ የጉልበትህን ላብ የትም የምትዘራ ትዕ ዛዙንም የማትከተልነህ ብለው አኮረፈኝ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ተለያየን ።

ጋብቻም ሆነ ልጅ ከእግዚአብሒር የሚገኝ በረከት ነው ። እነሆ ልጆች የእ ግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው መዝ 126 127 ቁ 3

ባልና ሚስት በመፈቃቀርና በመተሳ ሰብ እስከ ዕድሜአቸው ፍጻሜ ድረስ የኖ ሩበትን የጋብቻ ዘመን እንዲህ ቢያስላ ስሉት ብልጫውን ለአንባቢዎች እንዲ ወስኑት እተዋለሁ ሲሉ ያላቸውን ማጠቃ ለያ ሃሳብ ሰጥተውናል ።

የአቶ ፋንታዬና የወ ሮ እጅጋየሁ ሰላም የመላበትንና የተባረከውን ጋብቻ ታሪክ ተመልክተናል ይኸም መልካም አርአያና ምሳሌነት ክርስቲያን ኅብረተ ሰብ ሁሉ ሊከተለው የሚገባ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ጊዜ ሳልጠቁም አላል ፍም ። እግዚአብሔር አንድ ያደረገውን ሰው አይለየውም ተብሎ ተጽፏል ።

## ይህን ያውቁ ኖሯል?

ከገጽ ፲፬ የዞረ

ስለሙሴ የመጨረሻ ቀን በመጽሐፍ ቅዱስ «የእግዚአብሔር ባርያ ሙሴ እን ደ እግዚአብሔር ቃል በዚያ በሞዓብም ድር ሞተ።በቤተ-ፌጎርም ፊት-ለፊት በሞዓብ ምድር በሸለቆው ውስጥ ተቀ በረ ። እስከ ዛሬም ድረስ መቃብሩን ማ ንም አላወቀም ። ዘዳ . ምዕ .34 5 -6 ተብሎ ተጽፏል ።

ዜና አይሁድ ግን ፣ «... ምንም እንኳ ሙሴ እንደሞተ በአሪት መጻሕፍት ቢጻ ፍም « ይልና » «ሙሴ የእሥራኤልን ሽማግሌዎች ካሰናበተ በኋላ ኤሊዛርንና ኢያሱን አቅፎ ስሞ ደህና ሁኑልኝ ለማ ለት እጁን እንደዘረጋ ንግግሩን ገና ከአፉ ሳይጨርስ፣በድንገት ደመና ጋረዳቸው ወደ አንድ ሸለቆ ተሰወረ ። ምንም እንኳ በሙሴ መጻሕፍት ሙሴ እንደ ሞተ ቢጻፍም በእርግጥ ሞቷል ማለት አይደ ለም ። እጅግ - ሲበዛ ባለሟል ስለነበር ወደ እግዚአብሔር ሄደ ተብሎ እንዳይ ነገርለት ስለፈለገ ፣ ለትሕትና ሲል ተጋኖ እንዳይነገር የተደረገ ነው » ይላል ።



www.ethiopianorthodox.org

## የከንባታና ሐዲያ....

ከገጽ ፮ የዞረ

ሎች ወደልጅቱ ዘመዶቹ ተልከው በሚ
ያቀርቡት ልመና የሚከናወን ሲሆን ሁ
ለተኛው የጋብቻ አይነት ደግሞ ልጁ
ና ልጅቱ በሚያደርጉት ስምምነት
የወዶ ገብ ጋብቻ ነው ። በቃል ኪዳን
ለሚደረገው ጋብቻ ወንዱ ልጅ ለሴ
ትዋ እጮኛው ብዙ ጥሬ ገንዘብ ወ
ይም የቁም ከብት ጥሎሽ ይከፍላል ።
አልፎ ተርፎም ወላጆችዋን ትልቅ
ቡሉኮ ፣ ከተጠየቀም ያንበሳ ወ
ይም የነብር ቆዳ ለምድ ይሸልማል ።
ልጅቱንም በሠርጉ ቀን ሙሉ ጌጣጌ
ጥና ልብስ ያለብሳል ለሠርጉ የሚሆን
ዲል ያለ ሠርግ በሁለቱም ወጣቶች ወላ
ጆች ቤት ይደገሳል ። ጠላ በያይነቱ
ጠጅ ከምግብም ተውጣጥቶ በዛ ያለ
ዓይነት ይዘጋጃል ። በዕለቱ ወጣቱ ታጅ
ቦ ወደ ሙሽሪት ቤት ይመጣና ውሎ -
ገብ ከሆነ ሠርገኛው በሌቶ ጠጥቶ ሆ
እያለ ልጅቱን ይዞ ወደ ሰፈር ይመለሳል
የሚሰነብትበት ሠርግ ዓይነት ከሆነ ሠ
ርገኛው ተዝናንቶ ሲስተናገድ ይሰነብ
ትና በተፈቀደለት ቀን ሙሽራዋን ይዞ
ይመለሳል ። ሙሽራዋ ከወላጆችዋ ተሰ
ናብታ ስትሄድ ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ
ቁሳቁሶችና ከብቶች ለጎጆ መውጫ
ይሰጧታል ።

በከንባታና ሃዲያ አውራጃ የአንድ
ሕፃን ልጅ መወለድ ለቤተሰቡ ትልቅ
የደስታ ምንጭ ነው ። እንዲት ነፍሰ
ጡር ሴት የመውለጃዋ ጊዜ ሲቃረብ ም
ቾት በሚሰጥ ሥፍራ በተለይ እሳት ዳር
መኝታ ይዘጋጅላታል ። ጉዝጓዝ ተደል
ድሎ ከግራና ከቀኝ ድጋፍ ተሠርቶለት
በላዩ ላይም ሽልም ቁርበት ይነጠፍና
እንደ ቤተሰቡ ችሎታ ከላይ የሚደረብ
ልብስ ትለብሳለች ። ነፍሰጡሯ እንደተ
ገላገለች አዋላጆችና ጐረቤቶች የቡላ
ሾርባ ይጋበዛሉ ። ከእንሰት ከሚገኘው
ከቡላአ የሚዘጋጀው ገንፎ ለጤና ተስ
ማሚና ብርታትን እንደሚሰጥ ይታወ
ቃል ። ከመጠጥም እንደዚሁ ሴሎ
(ሻአሜታአ) ቃሪቦና ጠላ ተዘጋጅቶ
ለደስታው ተካፋዮች በሙሉ ይቀርባል
ለወላዲ የሚሰጠው ምግብ ግን ከዚህ
ለየት ያለ ለሰውነቷ የሚስማማ ዓይነት
ነው ። ለተወለደው ሕፃንም ከፍተኛ
ጥንቃቄ ይደረግለታል በወለደች በሦስ
ተኛው ቀን ቅቤ ትቀባለች ። ይህም ወ
ላዲን ለመመረቅ የተሰበሰቡት ሴቶች
እንደችሎታቸው ቅቤ ይዘው በመም
ጣት እናቷ ላይ ያስቀምጣሉ ። እንደ
ቅቤው ርጥብ ሁኚ በማለት ይመርቋታል
እስከ ሶስት ቀን ድረስ ለወላድ ሆድ
የሚስማማ ነው ብለው የሚያምኑበትን
ልዩ ልዩ ለስላሳ ምግቦች ይመግቧታል፡
ከዚያም የፍየልና የበግ ጠቦት እየታ
ረደ "ሱልሶ" (ክትፎ) በቅቤ የተለወ
ሰውን ትመገባለች ። አልፎ አልፎም
ጭኮ በወተት ትመገባለች ። ወላዷን
የምትጠይቅ ሴት በልጉም ጮጮ ወይ
ም (በጭንቆአ) በቅቤ የተመታ ወተት
እያመጣች ራስጌዋ በቆመ እንሥራ ወ
ይም ገች ስለምትሞላ ወላዲ የወተት
ችግር የለባትም ።

እመጫትዋ በተገላገለች በአሥራ
አምስተኛው ቀን የመመረቂያ ቀን ስለ
ሆነ በቤተ ዘመዱ የሚዘጋጅ "ወበጣ"
የተባለ በዓል አለ ። በዚህ በዓል ላይ የ
ሚሳተፉት ሴቶች ብቻ ናቸው ። እያንዳ
ንዷ ሴት ለበዓሉ የሚያስፈልገውን ም
ግብና መጠጥ በበጐ ፈቃደኝነት እንዳ
ቅሟ ይዛ ትመጣለች ። ከዚያም ያ ሁሉ
ምግብና መጠጥ ዓይነት በዓይነት በአን
ድነት ከተቀላቀለ በኋላ ሴቶች ሲበሉ ሲ
ጠጡ ሲዘፍኑና ሲመርቁ ውለው ይለያ
ያሉ ። በከንባታና ሀዲያ የቀድሞ ባህል
ውስጥ ከፍተኛ ግምት ይሰጠው የነበረ
ሥነ ሥርዓት ግዝረት ነው ።

የሴት ወይም የወንድ መገረዝ ከፍ
ተኛ ደረጃ ስለሚሰጠው ከሠርግ ጋር
ተመጣጣኝ የሆነ ድግስ ይዘጋጃል ።
በከንባታና ሃዲያ ልጆች የሚገረዙት
ትልቅ ከሆኑ በኋላ ነው ። ልጆቻቸውን
ሳያስገርዙ የሚያቆዩትም ልጆቹ በደ
ንብ ተመግበው ጠንካሮች ከሆኑ ሲገ
ረዙ ብዙ ደም አይፈሳቸውም የቁስሉም
ሕመም አይበረታባቸውም በማለት
ነው።አብዛኛውን ጊዜ ግዝረት የሚከ
ናወነው ከነሐሴ እስከ መስከረም ባለ
ው ወቅት ነው ።

የድግሱም ዝግጅት የሚጀመረው
ከመገረዣው ዕለት ሐያ ቀናት ያህል
ቀደም ተብሎ ነው ። በዝግጅቱም ወ
ቅት ጐረምሶችና ልጃገረዶች ተሰብስ
በው "የርቤ" በምትባለው ትንሽ ድቤ
በመታጀብ "ኡዋዬ" እያሉ እንኳንስ
ተጫዋቾቹን ይቅርና ተመልካቹንም
በከፍተኛ የሙዚቃ ስሜት የሚያወዛው
ዝ ዘፈን ይዘፍናሉ በዚህ ደማቅ ጨዋታ
ጊዜ ልጃገረዶችና ወንዶች በግጥም
ለመሞጋገስና ለመወቃቀስ ዕድል ይ
ኖራቸዋል ። የግዝረቱ ጊዜም እየተቃ
ረበ ሲሄድ የዚያኑ ያህል ጨዋታው እየ
ደመቀ ይሄዳል ለግዝረት ጊዜ የሚዘጋ
ጀው የምግብና የመጠጥ ዓይነት ብዙ
ስለሆነ የሚመጣው ሰው ሁሉ እንደ
ልቡ ሊመገብ ይችላል ። የግዝረቱ ቦታ
የተለየ ከፍታ ያለው መደብ ነው ። በግ
ዝረቱም ዋዜማ ተገራገሮችን የሥቃይ
ሐሳብ እንዳይገባቸው ለማረሳሳት ባል
ንጀሮቻቸው ደማቅ ጨዋታዎች እንደ
"ካበልባቦቶ" ያለውን ሲዘፍኑና ሲጫ
ወቱ ያድራሉ ሲነጋጋ ሲል የመገረ
ዣው ሰዓት ምልክት የሆነች የሀሐይ
ጮራ ትጠበቃለች ። የሀሐይ ጮራ
ብቅ እንዳለች የሚገረዘው ሰው ወደ
ተዘጋጀለት ሥፍራ ሲያመራ ፍርሀቱን
ለማረሳሳት ሲዘፍኑና ሲጨፍሩ ያደሩ
ት "ኮረዶች" ሀቦሬ ፣ ሀቦሬ" የተባ
ለውን ልዩ ስልት ያለው እንጉርጉሮ
ይጫወታሉ ። ትርጓሜውም ጀግና ሁን
አትፍራ ሰው እንዳይስቅብህ ሰው እንዳ
ይስቅብሽ ማለት ነው ።

የመገረዙም ተግባር እንዳበቃ የተገረ
ዘውን ሰው ከደሙ ላይ አንስተው ሙ
ቀት ሊያገኝ ወደሚችልበት በተለይ
ምድጃ ዳር በተዘጋጀው መደብ ላይ ያስ
ተኙታል ። ከዚያም በብዛት ወተት እን
ዲጠጣ ይደረጋል ። የሚገረዘው ሰው
ደረቱና ጭኑ ቅቤ ይቀባና ለተሰበሰበው
ቤተ ዘመድ ሁሉ ተዳርሶ የምረቃው
ሥነ ሥርዓት ይጀምራል ። ምርቃቱን
የሚቀበሉት የዓይን አባት ወይም የዓ
ይን እናት ወይም ወላጅ እናት ናቸው ።
የዓይን አባት ወይም የዓይን እናት ማለ
ት የሚገረዘውን ሰው ዓይን በሚገረዝ
በት ጊዜ እንዲያው ለወግ ሸፈን የሚያ
ደርጉ ናቸው ። በምረቃው ሥነ ሥርዓት
ጊዜ ምርቃን ተቀባዮች በቅል የተሞላ
ሻሚታ (ቦርዴ) ይዘው ወደ እያንዳንዱ
ተጋባዥ ቀረብ ሲሉ መራቂው የተሞላ
ውን መጠጥ መልሶ ይሰጣል ። ምርቃት
ተቀባዩ ይቀምስና ለመራቂው መጠ
ጡን ይመልሳል ። ይህ ሙሉ መጠጥ
በምረቃው ጊዜ የሚቀባበሉት "ሙሉ
ሁኑ ሙሉ ያድርጋችሁ" በሚል አስተ
ሳሰብ እንደሆነ ይነገራል ። ከዚያም መ
ራቂዎቹ "የውሻ ቁስል ያድርግልህ"
በማለት ይመርቃሉ ። የውሻ ቁስል ያድ
ርግልህ ማለት ቁስሉ በተሎ ይዳንልህ
ማለት ነው ። ውሻ ቁስል አይጠናበትም
ስለሚባል የውሻ ቁስል ያድርግልህ
ይሉታል ማለት ነው ።

ለሚገርዘው ሰው ቅቤ ሻሚታ እንዲ
ሁም ጥራጥሬ እህል ወይም ገንዘብ ይሰ
ጡታል ። ግብዣውም ይቀጥላል ። የተገ
ረዘውም ሰው ሕመሙ እንዳይሰማው
ልዩ ልዩ ዘፈኖች ይዘፈንለታል ። ሶስ
ትና አራት "ዴታ" ክራር ዋሽንት በመ
ያዝ የአካባቢው ጐረምሶች ኮረዶች
ማታ ማታ የደመቀ ጨዋታ በመጫ
ወት ሥቃዩን እንዲረሳ ይደረጋል ። በከ
ንባታና ሃዲያ ባህል የግዝረት ጊዜ የተወ
ሰነ ጊዜ ስለሆነ በአንድ ሰሞን ብዙ ሰ
ዎች ይገረዛሉ ። ከግዝረት በኋላ "ነቃ
ታ" መሰነባበቻ ወደሚባለው ሥፍራ
ይሄዳሉ ። በዚህ ሥፍራ የግዝረኞች
ሹም የተባለው ለእያንዳንዳቸው ልዩ
ስም ያወጣል ። ስም የወጣለት ስሙን
ሊቀበል ተነስቶ በሚጨፍርበት ጊዜ
አንድ የሴት ጓደኛ ትቀርበውና አብ
ረው ይጨፍራሉ ። በጠባይ የምትስማ
ማው ከመሰለችው ጓደኛው ያደርጋ
ታል ።

### የሞትና የሃዘን ሁኔታ

በከምባታና ሃዲያ ባህል ሰው ሲሞት
ሃዘን ይጠነከራል ፀጦር ሜዳ ጀብድ
የሠራ ወይም በታታሪነቱ በህብረተሰቡ
መሃል የሚከበር ሰው ሲሞት ጋሻው
ጦሩ በልዩ ልዩ እቃዎች የተሸለመው
ፈረሱ ይወጣና ጦርና ጋሻ በያዙ ጓደ
ኞቹና ቤተዘመዱ እንዲሁም በሚያው
ቁት ለቀስተኞች ታጅቦ እየተፎከረ ጀ
ብድ ሥራው በይፋ እየተነገረለት ሬሳ
ው ወደ ማረፊያው ሥፍራ ይሸኛል ።
ኃዘን በደረሰ ቁጥር ሥራ ፈቶ ለብዙ ቀ
ናት መቀመጥ የተለመደ ነበር ። በተለ
ይም ሴቶች ባሎቻቸው ሲሞቱባቸው
ዓመትና ከዚያም በላይ በኃዘን ተቆራም
ደው ይቆያሉ ። በነበረው ልምድ ወንድ
እንጂ ሴት ልጅ ያባትዋን ንብረት የመ
ውረስ መብት እንዳልነበራት ሁሉ ባል
የሞተባት ሴትም የንብረትዋ ባለቤት
መሆንዋ ቀርቶ የባልዋ ወንድም ይወር
ሰዋል ።

### በአሁኑ ጊዜ

በባህል ተሐድሶ ዘመቻው እንዲሁም
የመሠረተ ትምህርቱም ሂደት እየተስ
ፋፋ ስለሆነ በከምባታና ሃዲያ አውራጃ
በአጉል እምነቶችና በኋላ ቀር ባህል
ላይ ዘመቻ እየተካሄደ ነው ። በዚህም
ሳቢያ በቤተሰብ አቋም በጋብቻ በሞ
ትና በኃዘን በሥራው ላይ እንቅፋቶች
የሚሆኑ አጉል ባህሎች ሁሉ እንዲቀሩ
ትምህርት የሚሰጥ ሲሆን የብሔረሰቦ
ቹን ማኅበራዊ አቋም ደህና አድርገው
የሚተረጉሙ ተደጋፊ ባህሎች ደግሞ
በተሐድሶ እንዲደራጁ በመደረግ ላይ
ነው ። ስለሆነም በአውራጃው ውስጥ
በያጋጣሚው በብሔረሰቦች መሃል የሚ
ደረገው የባህልና ኪነጥበባት ውድድር
ምሥክር ነው ።

## ሙታን..

ከገጽ ፮ የዞረ

ዲሁም ኃጥአንን እናንተ ርጉማን ለሰይ
ጣንና ለመልእክቱ ወደተዘጋጀላቸው ገሃ
ነመ እሳት ሂዱ በማለት የመጨረሻ
ፍርዱን ያስተላልፋል ፣ ከዚያ በኋላ ጻድ
ቃን ወደ ዘለዓለም ሕይወት ኃጥአን
ግን ወደዘለዓለም ፍዳ ይሄዳሉ ማቴ 25.
31-46 ፤

ይህንንም በዮሐንስ ወንጌል ራሱ
ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ሲናገር "በመቃብር ያሉት ሁሉ
ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል
መልካም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ፤
ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይነ
ሣሉ" ብሏል ዮሐ 5. 25 - 29

ሙታን የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰም
ተው መቃብር ክፈቱልን መግነዝ ፍቱ
ልን እቀፉን ደግፉን ሳይሉ ተነሥተው
የመጨረሻው ዋጋቸውን የሚያገኙበት
ዕለት በክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት
ስለሆነ በዚያ ቀን ዓለም ሳይፈጠርዘመ
ን ሳይቆጠር ወደ ተዘጋጀችው መንግ
ሥተ እግዚአብሔር ገብተን በማይለ
ወጥ ዘለዓለማዊ ደስታ ለመኖር እንድን
በቃ እምነታችንን በእግዚአብሔር ላይ
አጠንክረን ሥነምግባራችንን አሳምረን
እንጠብቀው ።

ቁ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሩፋኤል

ሩፋኤል ማለት በዕብራይስጥ ቋንቋ እግዚአብሔር መድኃኒቴ ማለት ነው ሩፋ መድኃኒት ኤል እግዚአብሔር ማለት ነውና።2ኛም ሩፋኤል ማለት መስተፍሥሒ አልባብ ማለት ነው።ይኸውም ልቡናን ደስ የሚያሰኝ አስደሳች ያምላክ ደስታ ማለት ነው ። አስደሳችነቱም የሰውንና የእንስሳትን ማኅፀን ፈትቶ እንዲወልዱ የሚያደርግ ተራዳዒ መልአክ ነውና። ይኸውም መልአክ በመላእክት መዓርግ 3ኛ አለቃ ነው ። 1ኛ ሚካኤል 2ተኛ ገብር ኤል ፣ 3ተኛ ሩፋኤል ነው አሁንም እንደ ተናገርነው በመዓርግና በደረጃ 3ተኛ መልአክ ሲሆን በ 23ቱ ነገደ መላእክት ላይ የተሾመ መልአክ መሆኑን ደግሞም ከ 7ቱ ሊቃነ መላእክት 1ኛው መላክ እሱ መሆኑን ከ7ቱ የመላእክት ኣለቆች እኔ ነኝብሎ ለጦቢት ነግሮታል 3ተኛም ጳጉሜን 3 ቀን በተሾመበት ቀን የሹመትን ነገር በሚናገረው መጽሐፈ ድርሳኑ ይናገራል ።

በንዑስ ሰናክሬም ጊዜ ተማርኮ ነነዌ ለወረደው ለሄደው ለጦቢት ድንቅየሆነ ልዩ ታምራታዊ ምልክት ያደረገለት መላኩ ሩፋኤል ነው ለወለደው ልጁ ለጦቢያ ነግሮ በዓሣ ሐሞት የጠፋውን ዓይኑን አብርቶለታል ። ከዚህ አስቀድሞ ጦቢት ዓይኑ ጠፍቶ ሳለ ወደ ፈጣሪው ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አድርጎ ለመነ። ጸሎትም አቤቱ ጌታዬ ሆይ ድኅነቴንና ጠማዳሪነቴን አስብ አስበህም ይቅር በለኝ የኔንናያባቴንኃጢአት አስበህዕዳበደል አታድርግብን ለምርኮና ለዘረፋ ያደረግኸንን አስብ ። አቤቱ ፈጣሪዬ ሆይ አንተ ደስ የሚያሰኝህን ነገር በፊትህ አድርግ። ያም ባይሆን አንተ ይቅር ብለህ ዓይኔ የማይበራ ከሆነ ነፍሴን የሚቀበል መላክእዘዝ ሞቼ አፈር መሬት ልሁን ዓይኔ ጠፍቶ ከምኖረው ኑሮ መሞት ይሻለኛልና ብሎ ጸለየ ።

በዚያው ወራት ራጉኤል የሚባለውን ሰውዩ ልጅ ሣራ የምትባለውን ሴት ልጅ አስማንድዮስ የሚባል ጋኔን ድንገት ተቆራኛት ያዛት እሷንም እናት አባቷ ለ 7 ባሎች ድረዋት ነበርና ባሎቿም ወደ እሷ በቀረቡ ጊዜ በግብር ያደረባት ሰይጣን ሳይቆይ ( ሳይውሉ ሳያድሩ ) ይገድላቸው ነበር ።

እሷንም የእናት ያባቷ አሽከሮች አንች ወንዱን ሁሉ ፈጀሺው ይብላኝልሽ ከማን ጋር ልትኖሪ ነው ፣ እያሉ ያሽሟጥጧትና ያፌዙባት ይቀልዱባትም ነበር ። / ምሳሌ / ባል የሚሞትባት አንዲት ሴት እንዲህ አለች ይባላል። «ቀኑ ያጠረውን እያጋጥመኝ ሴቲቱን እንደ ወንድ ገዳይ አሰኙኝ » ። ሣራም ከፌዛቸውና ከስድባቸው እንዲያድናት ጧትና ማታ እያለቀሰች ወደ እግዚአብሔር ትጸልይ ነበረች ። ኋላም የጦቢትና የእሷ ልመና በፈጣሪያቸውና በአማላጁ በቅዱስ ሩፋኤል ዘንድ ደርሶ ተሰማ ። ያን ጊዜም ጦቢት ገባኤል ከሚባለው ሰው ዘንድ ያስቀመጠው ያደራ ገንዘብ(ብር) ስለነበረው ልጁን ጦብያን ጠርቶ ልጄ ሆይ በገንዘብ ተቀጥሮ ካንተ ጋር አብሮህ ወደ ገባኤል የሚሄድ አንድ ሰው ፈልገህ እባክህ አምጣ አለው አደራ ያስቀመጥሁት ብር ገባኤል ከሚባለው ሰው ዘንድ ስላለ ። እኔ ሳልሞት ይኸን ጊዜ ሄደህ አምጣ አለውና ጦብያም ያባቱን ነገር ሰምቶ ወደ አደባባይ ተነሥቶ ወጣ

ቢወጣ መላኩ ቅዱስ ሩፋኤልን በሰው አምሳል ተመስሎ በገንዘብ የሚቀጠር ሆኖ አገኘውና እባክህ አንተ ወንድሚ ገንዘብ እንሰጥሃለንና አብረኸኝ ወደ መንገድ እንሂድ አለው ። እሱም እሺ ብሎ አስደሰተው ። መልአኩም በሰው ተመስሏልና ጦብያ መላኩን ስምህ ማነው አለው-መልአኩም አዛርያ ይባላል አለው። አዛርያም ማለት ረዳት / ወይም ረድኤት ማለት ነው ።

ከዚህ በኋላ ካባቱ ተሰናብቶ መንገዳቸውን ቀጠሉ ሲሄዱ ውለው ማታ ጤግሮስ ከሚባለው ወንዝ ደረሱ ። ከዚያም በደረሱ ጊዜ ጦብያ እግሩን ሊታጠብ ( ለመታጠብ ) ከወንዝ ወረደ ። ወዲያው ታላቅ አምባዛ ዓሣ ከባሕሩ ውስጥ እየተንሣፈፈ ወደ ጦብያ መጣ ያን ጊዜ መላኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን በል አኃዞ ለዝኩ ዓሣ በል ይኸን ዓሣ ያዘው አይዞህ አትፍራ አለው ። ይዘህ ስታበቃ ልቡንና ሆዱን ሐሞቱን ጉበቱን አውጥተህ ያዝ አለው ። እሱም መላኩ እንዳዘዘው አደረገ ልቡን አንገቱን ፣ አሞቱን ጉበቱን አውጥቶ በመያዣ አስቀመጠው ። ከዚያ በኋላ መልአኩና ጦብያ ከራጉኤል ቤት በደረሱ ጊዜ ሣራና እናቷ በደስታ ተቀብሏቸው ። ይኸን ጊዜ ጦብያ የሣራን ቁንጅናና ደም ግባት የመልኳንም ማማር አይቶ ስለ ወደዳት ፣ ይህችን ልጅ አግብቼ አገሬ ልሂድ ብሎ አሰበ።አስቦም አልቀረ ልጁን እንዲሰጠውና (እንዲድርለት ) አባቷን ለመነው ። አባቷም እውነተኛ ደግ ሰው ስለሆነ ሳይደብቅ የልጁን ነገር ገልጦ ልጄ ሆይ የእሷን ነገር ሁሉ ያውቀዋል ፣ አገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ነው ። ይኸውና ከዚህ ቀደም ለ7 ባሎች ዳርኋት (አገቧት ) ሁሉም አሁን በሕይወት የሉም ሞተዋል አለው ። አንተ 7ኛ ነህ ወይም 7ቱ ሞቱ አንተ 8ተኛ ነህ አለው ።

ጦብያም የእግዚአብሔር ቃሉ ይሁን እግዚአብሔር ያውቃል አለው ደፈረ ማት ነው መሽቶ የመኝታ ጊዜ ስለ ደረሰ ከመኝታ ( ወይም ከሙሽራ ቤት ) ባገቧቸው ጊዜ ጦብያ መልአኩ ሩፋኤል የነገረው ነገር ትዝ አለውና አሰበ ። ያን የዓሣውን ልቡንና አሞቱን ጉበቱን ወስዶ አትኅልጉሎ አጤሰው ያን ጊዜ 7 ባሎቿን የፈጀባት ( የገደለባት ) አስማንድዮስ የሚባለው ጋኔን እንደ ጢስ ተኖ እንደ ጉም በኖ ጠ ጠፋላት ጦብያንም እግዚአብሔር ከሞት አዳነው ።

ከዚያም በኋላ ሄዶ ከገባኤል ዘንድ የነበረውን ያደራ ገንዘብ አምጥቶ በሙሽራ ስነ ሥርዓት 40 ቀን ሙሉ ቆይተው ወደ አገራቸው ተመልሰዋል ። ደስታውም ብቻ 40 ቀን ያስቀምጣል ። አባቱ ጦቢትም ስለ ቀሩበት ልጁን ምን አገኘው ይሆን እያለ ሲያወጣ ሲያወርድ ሲያዝን ነበረ ። እናቱም ሐና እንደዚሁ ስታዝንና ስታለቅስነበርና ሚስቱን ይዞ በሰላምስለመጣላቸው ደስታቸው ከልክ ያለፈ ሆነ። ከዚህ በኋላ ልጁ ጦብያ የዓሣውን አሞት አሟርሮ የአባቱን ዓይን ኳለው ( ቢኩለው ) ቦግ ብሎ በራለትና ዳነ የዓሣ ሐሞት ለዓይን መድኃኒት ነው እያሉ ብዙ ሰዎች እያማረሩ ይኳሉታል ። ጦቢትም ከልጁ በደህና ስለ ተገናኘ ዓይኔን በዓይኔ ያሣኸኝ ፈጣሪዬ ብሎ ደስ አለው እግዚአብሔርን አመሰገነ ። ከዚህ በኋላ ጦቢት (ይሄይስ ምጽዋት እምዘጊቦቱ ለወርቅ እንዲል) ወርቅን ሰብስቦና አከማችቶ ከመያዝ ይልቅ መስጠት መመጽወት እንዲበልጥና እንዲሻል ለልጁ መክሮ አስተምሮ ካበቃ በኋላ በ 158 ዓመት ዕድሜው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ አረፈ ። ወደ ጥንተ ነገራችን እንመለስና መላኩ ሩፋኤል ተቀጣሪ መስሎ በእግዚአብሔር ፈቃድ ጦብያን እንደረዳው ሁሉ እኛንም እንዲረዳን አውቀን አማላጅነቱን አምነን ብንለምነው ጸሎታችንን ይሰማናል ከፈጣሪው ያማልደናል ጸሕቀ ልቡናችንን ይፈጽምልናል ሐሳባችንን ይሞላልናል ለቴዎዶስዮስና ለዲዮናስዮስ የለመኑትን እንደ ሰጣቸው አሳባቸውን እንደፈጸመላቸው ሁሉ እኛም እንደ እነሱ ከጸለይንና ከለመን ፣ ጸሎታችንን ተቀብሎ ያማልደናል ። ታሪክ ቴዎድርስ በሮም መንግሥት እንዲነግሥ ለምኖት ንጉሥ አድርጎታል ። ዲያናስዮስም ሊቀጳጳሳት ( ፓትርያርክ እንዲሆን ለምነው በመንፈሳዊ ሹመት ፓትርያርክ አድርጎታልና።ሥጋዊ ሹመት ቢለምነው ሥጋዊ ሹመት የወደደውን ሰጠው (አሰጠው) መንፈሳዊ ሹመት ቢለምነው የወደደውን መንፈሳዊ ሹመት ሰጠው አሰጠው ይኸውም ታሪክ በድርሳኑና በስንክሣሩ ተጽፎ ይገኛል መልአኩ ሩፋኤል የተሾመበት ጳጉሜ 3 ቀን ስለ ሆነ ፣ ቤተ ክርስቲያኑ በተተከለበት ስሙ በተጠራበት ተገኝተን መታሰቢያውን እናክብር አሁንም የመላኩ ልመናና ምልጃ ከኛ ጋራ ይኑር ።

አባ ቸርነት ጋሻው በዛ

# አትናስያ...

ከገጽ ፲ የዞረ

ለሊት አባ ዮሐንስ ከበአቱ ሁኖ አትናስያ ካለችበት በአት የብርሃን መሰላል ተተክሎ መላእክት በዚያ መሰላል ሲወርዱና ሲወጡ ያያል ምንድነው ብሎ በሃሳብ ላይ እያለ ሲነጋ መልአኩ መጥቶ አባ ዮሐንስን ያቺ ያመጣሃት ሴት አርፋለች መቃብሯንም አንበሳ ቆፍሮ ልሃልና ወስደህ ቅበራት ለሊት መላእክት ሲወጡና ሲወርዱ ያየኸውም ነፍሷን ወደ ገነት ሲወስዱ ነው ሲለው አባ ዮሐንስ ቀጠል አድርጐ ለመሆኑ እግዚአብሔር ኃጢአቷን ይቅር ብሎላታል ? ብሎ ቢጠይቀው ሁሉን ነገር ትታ በተከተለችህ ጊዜ ነው ኃጢአትሽ ተሰረየልሽ ያላት ሲል መለሰለት ።

አባ ዮሐንስ ሐጺርም እንደታዘዘው አንበሳ በቆፈረለት ጉድጓድ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማሟላት አትናስያን ቀብሯታል ይላል ። ስንክሳር ነሐሴ ሁለት ቀን ።

እንግዲህ ከአትናስያ የምንማረው ቢኖር አባ ዮሐንስ ገብቶ ስለ ዓለም ከንቱነት እንዳስረዳት በአንድ ጊዜ ቃሉ ከሕይወቷ ጋር ተስማምቶ የተሠማራችበት ሥራ በእርግጥ ሕገ ወጥ መሆኑንወዲያውኑ ተረድታ በመጸጸት ምን ባደርግ ይሻላል ብላ መጠየቋ ራሱ ታላቅ ትምህርት ነው ።

ሁለተኛ ከታሪኳ እንደተረዳነው በግብረ ዝሙት የሰበሰበችውን ወርቅና ሃብት ሳትሰበስብ አደራ አስቀምጡልኝ ወይም እከሌ (እከሊት) ሃብቴን ይውረሱ ብላ ለማንም ሳታወርስ እንደ ደነገጠ ሰው በራ መውጣቷ ለኑዛዜ ጊዜ አለመስጠቷን ያስረዳናል ።

ሦስተኛው ዛሬ በጊዜአችን እንደሚደረገው ብዙ ሴቶች በውዴታ ወይም በችግር ምክንያት በሴትኛ አዳሪነት ሥራ ተሰማርተው ይቆዩና በመጨረሻ ሞት ሲያጣድፋቸው የንስሐ አባቴን ቶሎ ጥሩልኝ ልናዘዝ እግዚአብሔር ነፍሴን ይቅር እንዲላት ይህን ያህል ገንዘብ ለድሆች መጽውቱልኝ ሌላውን ለልጆቼ ለዘመዶቼ ብለው በማከፋፈል ቶሎ ሥጋ ወደሙ ተቀብሎ ሁሉም በቶሎ ቶሎ ያልቃል ። አትናስያ ግን በዝሙት የሰበሰብኩት ገንዘብ የኔ ገንዘብ አይደለም በሕገ ወጥነት ያገኘሁት ስለሆነ አይጠቅመኝም ። ለእግዚአብሔር ብሰጥም እግዚአብሔርበኃጢአት ገንዘብ አይደሰትም ለድሆች ብሰጠው ለፍቼ ደክሜ ያገኘሁት ባለመሆኑ የሚረዳኝ አይመስለኝም ብላ ይቅርታን በአብራኩ ሕሊናዋ ጠይቃ መከተሏ ታላቅ ትምህርት ሊሆነን ይገባል ።

ከዚህም ሌላ የአትናስያ ታሪክ ብዙ ነገሮችን ያስታውሰናል 30 ዓመት ሙሉ ሲቀማ የኖረውን ሰው እምነቱን አይቶ ሁለት ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ኃጢአቱ የተሰረየለትን ወንበዴ እናስታውሳለን ። ማርያም መግደላዊት እንባዋን እያፈሰች በፀጉሯ እግሩን ስታጥበው እውነተኛ ይቅርታ ፈላጊ መሆኗን ተረድቶ ወዲያውኑ ኃጢአትሽ ተሰረየልሽ ያላትንና ሌሎችንም ሁሉ እናስታውሳለን ።

አትናስያ በኃጢአት ምክንያት ከምትወደው ጥሩ ሥራዋ ርቃ ነበረች ከእግዚአብሔርም ተለይታ ነበር ። መንፈሷ አስተሳሰቧ ሁሉ ስለዝሙት ስለ አለማዊ ኑሮ ብቻ ነበር ። ግን እግዚአብሔር ምንም እንኳ እርሷ ከጊዜ በኋላ የኃጢአት ተገዥ ብትሆንም እርሱ ፍጡሩን ጭራሽ አልተዋትም ነበርና ከዚያ ከፉ ሥራ ሊያላቅቃት ችሎታ ስላለው ፈቃዱ ሆና አላቀቃት ።

ፈጣሪያችን ምሕረትና ይቅርታ ልማዱ ነው እኛም ኃጢአታችንን አውቀን ይቅርታ ከጠየቅነው ያለምንም ቀጠር ወዲያውኑ ይቅርታ ያደርግልናል ። ስለ ዚህ የይቅርታ ቀን ዛሬ እንጂ ነገ ስላል ሆነ ዛሬውኑ ቀርበን ይቅርታን እንጠይቅ ።





www.ethiopianorthodox.org

## እናትነት...

ከገጽ ፳ የዞረ

በምሥራቅ በኩል አዲስ ቤት ተቆልፋ (ተዘግታ) ቀይ ጉልማሳ ቁልፉን ሳይከፍት በዝግ በር ገብቶ በዝግ በር ሲወጣ አይቷል ። የተቈለፈች አዳራሽ የእመቤታችን ሳይከፍት ገብቶ ሳይከፍት የወጣው የክርስቶስ ቁልፍ የማኅተመ ድንግልናዋ ምሳሌ መሆኑን መምህራን ያስረዳሉ ባለ ራእዩ ያየውና የሰማው የሚከተለው ነው ። "ወደ መቅደስም ወደ ሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበር፤ እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" ሕዝ 44 ፣ 1 - 3 ።

ይህንና የመሳሰለውን ትምህርት ተቀብለን የቀደሙንም አባቶች እንዳስተማሩን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ እናት እንደሆነች በእናትነትዋም ላይ በድንግልና ጸንታ እንደኖረች እናምናለን እናሳምናለንም ። አምላክን በድንግልና የወለደች ቅድስት ማርያም በንጽሕና በድንግልና ያጌጠች በነፍስና በሥጋ በነቢብና በገቢር በርእ
ስና በሥጋ በነቢብና በገቢር በርእ
ፍእ ፣ በነፍስ በሥጋ ድንግል ናት በንጽሕና በድንግልና ለመኖር የነበራት ጽኑዕ ሕሊና የአምላክ እናት ለመሆንና በድንግልናም ጸንታ እንድትኖር አበቃት ። በዚህም "መትሕተ ፈጣሪ መልዕልተ ፍጡራን ከፈጣሪ በታች ከፍጡራን በላይ" ሁና ስለ ሰው ልጆች ደኅንነት የምትማልድ የክርስቲያኖች መመኪያና የደኅንነት ምልክት ሆነች ።

እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም ነፍስና ሥጋን ተዋሕዶ ሰው ሆነ ስለእኔም በደል በመስቀል ተሰቅሎ ስለ እኔ ሞተ በእርሱ ሞት የእኔ ሕይወት ተገኘ ብሎ የሚያምን ሁሉ ቅድስት ማርያም ክርስቶስን ከመጽነሷ በፊት በጸነሰችውም ጊዜ ከጸነሰችውም በኋላ ከመውለድዋ በፊት በወለደችውም ጊዜ ከወለደችውም በኋላ ድንግል እንደሆነች ማመን ይገባዋል ። አምላክ በተወሰነበት ማኅፀን ፍጡር ሊወሰንበት አይገባምና ስለዚህም ነው የእግዚአብሔር ቃል "ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ገብቶበታልና ተዘግቶ ይኖራል" በማለት ከጽንስም በፊት በጽንስም ጊዜ ከጽንስም በኋላ ፣ ከልደት በፊት በልደትም ጊዜ ከልደትም በኋላ ማኅተመ ድንግልናዋ እንዳልተለወጠና እንደማይለወጥ ያስረዳው ።

ስለዚህ ድንግል ማርያም ለሴቶች ጠባይ በማይስማማ ሁኔታ አምላክን በድንግልና ጸንሳ በድንግልና የወለደች ከእናትነትም ጋር ድንግልናን አስተባብራ የያዘች አማናዊት ድንግል ናት ።

ራ.ያ. አስረስ

## ከቤተክርስቲያን....

ከገጽ ፲፮ የዞረ

ም የከፋንና የኢሉባቦርን አህጉረ ስብከት እየተዘዋወሩ ጐብኝተው መንፈሳዊ ምክርና መመሪያ ሰጥተዋል ።

14ኛ ከየካቲት 12 - 20 1973 ዓ.ም የወለጋን ሀገረ ስብከትና በአሶሳ አውራጃ በሰፈራ ጣቢያ የሚገኙትንም ምእመናን ጐብኝተዋል ። በዚህም ወቅት በየሰፈራ ጣቢያው የተሠሩትንና በመሠራት ላይ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል ። ምእመናኑንም አጽናንተዋል ።

መጋቢት

15ኛ መጋቢት 26 ቀን 1973 ዓ.ም. ስብከተ ወንጌል የሚስፋፋበትን መንገድ የሚያጠና አንድ ከፍተኛ ጉባኤ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌል አዳራሽ ተቋቋመ ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ጉባዔውን በጸሎት ከፍተዋል ። ቅዱስነታቸውም ጉባኤውን በጸሎት በከፈቱበትና መመሪያ በሰጡበት ወቅት ፣ የቤተ ክርስቲያን መሪያዋ ወንጌል ተቀዳሚ ተግባርዋም ስብከተ ወንጌል መሆኑን ለጉባኤው አስረድተዋል ።

ሚያዝያ

16ኛ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሚያዝያ 18 ቀን 1973 ዓ.ም. የተከበረውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በዓል ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ቡራኬና ቃለ ምዕዳን በራዲዮና በቴሌቪዥን አስተላልፈዋል ።

ግንቦት

17ኛ ቅዱስነታቸው ከግንቦት 3 - 10 ቀን 1973 ዓ.ም፡ በጐጃም ሀገረ ስብከት ሰሜናዊ ክፍልና በደብረ ማርቆስ አካባቢ የሚገኙትን ታላላቅ አድባራትና ገዳማት መንፈሳውያን ትምህርት ቤቶችንና ድርጅቶችን ጐብኝተዋል ።

ሰኔ

18ኛ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሰኔ 2 ቀን 1973 ዓ.ም. ለእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የአንድ መቶ ሁለት ሺህ ብር ርዳታ አስረክበዋል ይኸው የርዳታ ገንዘብ የተገኘው ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላይ ምክር ቤት የድንገተኛ አደጋ መርጃ ክፍል ሲሆን ገንዘቡን ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እጅ የተረከቡት ጓድ ተስፋዬ ብርሃኑ የርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ናቸው ።

ሐምሌ

19ኛ/ ሐምሌ 12 ቀን 1973 ዓ.ም. ቅዱስነታቸው 3 ኤጲስ ቆጶሳትን ሾመዋል ። በዚሁ ዕለት ቅዱስነታቸው ለ 17 ኤጲስ ቆጶሳት የሊቀ ጳጳስና ማዕረግ ሰጥተዋል ።


www.ethiopianorthodox.org